አውቀን እንታረም

አቢይ አበበ
(ሌ/ጀኔራል)

፲፱፻፺፭ ዓ.ም.

አሥመራ - በ « ኢል ፖሊግራፊኮ ሶ. አ. » ታተመ ።

ሁለተኛው እትም ፲፱፻፺፯ ዓ. ም.
አዲስ አበባ - በቼምበር ማተሚያ ቤት ታተመ ።

በ፲፱፻፶፯ ዓ. ም. በአሥመራ ከተማ የመጀመሪያው እትም ታተመ ።

በሕግ መብቱ የተጠበቀ ነው

From the Library of

ፍሥሐ ኣጥላው ወልደ ዮሃንስ

FESSEHA ATLAW WOLDE YOHANNES

ሁለተኛው እትም ፲፱፻፷፯ ዓ. ም.
አዲስ አበባ በቸምበር ማተሚያ ቤት ታተመ ።

መ ቅ ድ ም ።

ሀገር ያለ ሰው ምድረ በዳ ሆኖ ትኖር ይሆ ናል ። ሰው ግን ያለ ሀገር ሊኖር አይችልም ።

ሀገር ምን እንደሆነች ሁላችንም እናውቅለን ነገር ግን ሀገር የምትኖርበትን ዘዴ ገና አጥርተን ያወቅነው አይመስለኝም ። ስለእዚህም የአንድ ሀገር ሰዎች መሆናችንን እንድናውቀውና ለአንድነታችን መጠጊያ የሆነችውን እናታችንን ኢትዮጵያን ለማገ ልገል ለማኖርና ለኑሮአችንም ለመሥራት የምንች ለው በአንድ መንፈስ ስንሰለፍና በንጹሕ ሕሊና ፀ ንተን ስንተባበር ብቻ ስለሆነ ወደ እዚህም በቅን ነት እንድንራመድ ስለሚአሻ የየአንድ አንዳችን መንፈስ ከደከማነት ወደ ጽኑነት መለወጥ አለበት ።

መተዛዘንን ፣ መተሳሰብን ፣ ጠንካራ መንፈስን ፣ ቅን ባሕርይን ፍቅርን እርስ በእርሳችን መተዋወቅንና አለመናናቅን ማወቅ ይገባናል ። ይህም በመሀከላ ችን ከሌለ ምንም ሊኖር አይችልም ። ወደ መጥፎ መንፈስ የሚመራ ሁሉ መጥፎ ነገሮችን እያራባ ሌላውን ሁሉ ከትቦ እንዳይጐዳ ያሠጋልና በኑሮ ውስጥ ምን ምን እንዳሉ ተረድቶ ከአሁኑ መገታት ያስፈልግ ይመስለኛል ።

በአጭሩ ከገለጥኩ በኋላ አስፋፍቶ ማተቱን የሚመለከተው የአንባቢዎች አእምሮ እንደሚሆን በማመን እተወውአለሁ ።

ለመልካም ሥራ ይውል እንደሆነ በማለት ተስ ፋ ይህን ትንሽ መጽሐፍ ለውድ ሀገሬ ሰዎች አበረክታለሁ ።

ዓለም።

ዓለም ገና ልጅነት አውራጃዋም ደግሞ
እርጅቱ የሚሞተው ሰው ብቻ ነው ቀድሞ።
ብዙ አሳልፋለች ብዙዎች ተከታ
የሁሉንም ምግበር በየተራው አይታ።
ዙፋ ምጥ ሲይዛት መውለዷም ሣይቀር
የእርሷ መገላገል ሰው ወልዶ መቅበር።
መሆኑን ስታውቀው በጣም ስትረዳው
እይዋት ስትቸል ወዴ ምት ስትነዳው
ሁሉም በበኩሉ እዜ አለሁ እያለት
መቄጂት በዘና በእዚህ ሰላም የሉት።

አ. አ

መ ነ ሻ ።

«ሰው የሴት ልጅ ጥቂት ቀን ይኖራል ሁከትም ጸገ
በ እንደ አበባ ይወጣል ከዚያ በኋላም ይረገፋል
እንደጽላም ይኩበልሳል አይቆምም»

ኢዮብ ም. ፲፬

ብዙ ጊዜ ሰውነቴ ዕረፍትን ይሻል ሰውነቴና መንፈሴ ተለያይተው የሚፈልጉትን ለመረዳት አቃ ተኝ ። ሌላ ተጨማሪ አእምሮ እንኳ ቢኖረኝ ልረዳው እችል አይመስለኝም ። እንደዚህም ስለአልኩ አንደ እንስሳ አትቍጠሩኝ በእናንተም ሆነ በሌላው ሰው ሊደርስ የሚችል ነገር ነውና ።

አንዳንድ ጊዜ ሁሉን ሳመዛዝን ሳወጣ ሳወርድ እዚህ ምን አደርጋለሁ እስከመቸስ አለሁበት እቆያ ለሁ ጨረቃና ፀሐይ ሲፈራረቁ ማየት የሰው ልጅ ሁሉ ወግ ነው ዛሬን አስመሽቼ ነገን ማንጋቴን አላ ውቀውም በእዚህም ምክንያት ብተክዝና የአለኝን ጊዜ ንቄ በሳልፈው አይሻልምን እላለሁ ።

በሌላው ጊዜ ደግሞ ለምን እተክዛለሁ በአለሁ በት ዓለም እምኖረው በጣም ለአጭር ጊዜ ነው ስለምን ደስ ብሎኝ አላሳልፈውም ለምንስ እንደሌ ላው ሁሉ አልሆንም! ስለ ሰውስ ብዬ እራሴን ለምን አስቸግራለሁ እኔ በለሁበት ጊዜ ያሰኘኝን ሁሉ አድርጌ ማለፍ ነው ። ሌላው የሚአደርገውን ሁሉ ለማድረግ እኔም ይቻለኛል ሰው መሬትን ያጣል እንጅ መሬት ሰውን አታጣም የእኔም ዕድል በግድ ከእዚሁ ጋር የተያያዘ ነው እያልኩ አስባለሁ ።

እንግዲህ በየአይነቱ እየጠቀሰ ኑሮየን የሚአዘ በራርቀውን ሕሊናየን የግል ጓደኛ አድርጌ መያዝ ግዴታ ሆኖብኝ እንደሌላው መሰሌ ሁሉ ይዠው እኖራለሁ ።

ልዩ አስተያየቴን ይዠ አራሴን እራሴ በመ ራው ማስኬድ ስመኝና ሲገባኝ የአለስሚ እየጠሩኝ የአለ ሥራየ እየቀበሩኝ ወገኖቹ መኖርን ስለአስጠ ሉኝ ሰው የሆነ ሰው እኔን ሌላውን ሰው በአስባል ታና በሽሙጥ በሐሰትና በተንኰል ይህንን በመሰሰ ሉት ሁሉ በማስመረሩ ከሰው ተለይቶ መኖር ቢአ ቅተኝም ሰው መሐል ሆኜ ሰውነቴንና ሰውነትን ንቁ እስከ ጊዜው እንከረፈፍአለሁ ።

ሰውነቴን ወይም ሰውነትን ስንቀው በኅርአያ ሥላሴ መፈጠርን ክጇ አይደለም ። እንደሰው ሁሉ አስበለሁ ሰውነቴንም ይዠ እንከራተታለሁ የሚአ የኝ ሁሉ ሰው ይለኛል እኔ ግን አምብዛም በሰው ነቱ አልመካበትም ።

ከብዙ ጊዚያት ጀምሮ ሰውንም ታገሠውአለሁ አጥርቼም ተመልክቸ ተመራምሬውአለሁ ወደየትም እንደሚመራ የት እንደሚደርስም ተረድቸውአለሁ ። የየራሱን ጉዘና ማረፊያውንም ሰው ሁሉ ያውቀ ዋል ግን አጥርቶ አይረዳውምና ሰው መሆኑን አክ ብሮ ለጊዜው ይኖራል ።

ሰው ሆኖ መፈጠር ሰውነትን ለማክበርና ምድ ርን ለመሙላት ብቻ ሣይሆን ትእዛዝትን ለማክበ ርና ሕግጋትን ለመፈጸም እንደዚሁም እውነትንና ትክክለኛ መንገድን ተከትሎ ከልብ ለመፈቃቀርም በሆነ ነበር ።

ግን ሰው ተብሎ እንዲፈጠርና በምድር ላይ እንዲኖር አስፈልጎ ተፈጥሮም መፈትን የሠፈረባት ሰው ደጉንም ክፉውንም ነገሮች ሁሉ አስክትሎ ዓለምን ወረራት ። በጊዜአችን ሲደረግ የአምናየው ሁሉ ምድር ከተፈጠረች ጀምሮ አስከ አለንበት ጊዜ ድረስ የነበረውን እንጅ ብርቅ አድርገን የምን ቆጥረው እምብዛም እንደሌለ እንመን ።

በተቀደሰ መንፈስ ለተቀደሰ ሥራ የተፈጠረው ሰው በበኩሉ ክፉ ስራዎችንና ተንኰልን እራሱ ፈጥሮ ሲጨነቅና ሲንገላታ ሲበሳጭና ሲያማርር ሲአዝንና ሲተክዝ ሰውነቱን ሲጠላና የተወለደበ ትን ቀን ሲረግም በወገኑ ላይ ሲያፈዛዝና ወንድሙን ሲገድል በጓደኛው መንገድ ላይ ወጥመድ ሲዘረጋ በጐሮቤቶቹ ሲቀና በሌላው ሲመቀኝ የጊዜውንና የራሱን ጥቅም ብቻ ሲከተል ዝርያውን በሐሰት ሲወነጅል የራሱን ሥራ ብቻ ሲያመሰግን ከአጠ ገቡ እራቅ የአለውን ሲያማና ሲንቀፍ እራሱን እያ ታለለ ሌላውን ሲአሳስት ተቆጥሮ የማያልቀውን ስንቱን ጉዳጉድ አመርቅዘና ደብቆ የያዘው ሰው እንደናንተም እንደ እኔም የአለ ነው ።

ሰው ፡ የተፈጠረበትን ልዩ መብት የራሱ የረ ከሱ ጠባይና ተግባር ተንኩሰው ስለአናንተ መከ ራው እሳዩ ላይ ተንዶበት ከአርሱም ላይ የሚነ ሡት ተወሰኰች ዝርያውን እየነደፉ አዳርሰውታ ልና ተጋቦቱም እስከ ዘለዓለም ተፈራራቂ ትውልዱ ይተላለፋል ። ወሮዶም ያደረገው ነገር ቢሆን ሳይ ወድ ጭንቅንና ፍርሃትን ተጨናጽፎ እስከ ተወሰነ ለት ጊዜ ድረስ እንዲዳክር ተፈርዶበታል ።

ሰው ሁሉ ተገልጦ ከሚታይበት ሌላ የማይ ታይ ቁራኛ ጠባይ ስለ አለው ከዚያ ሊያላቅቀው የሚችል ነገር አይኖርም ስለ እዚህም የእራሱ ተገ ዥ ለመሆን ተገድዶ ይገኛል ።

እያንዳንዱ ነገድ የተመራበት የዓለም ክፍል የሆነውን ምድር የሚአረኩ ሁለት ምንጮች ይገ ኛሉ እነዚህም የምሬትና የመጣፈጥ ጣዕምን የአፈ ልቃሉ ። እንግዲህ በክፍለ ምድሩ የሠፈረው የሰው ዘር በማይታየው ቁራኛ ጠባይ እየተመራ በምሬትና በመጣፈጥ የተከፈለችውን ዓለሙን መፈንጫው አ ድርጐ አንድ ጊዜ ከመራራው አንድ ጊዜ ከጣፋጩ እየተጐነጨ እንደ ለማዳ አውሬ ሲበርቅ ይገኛል ።

በምሬትና በመጣፈጥ ስለተከፈለችው ዓለም ብዙውን ነገሮች ሌላውም ሁሉ ስለሚረዳው ለም ሣሌ ያህል በጣም ትንሹን ልገልጠው እወዳለሁ ።

ትላንትና ደስ ብሎህ ነበር አሳብህም ፍላጐት ህም ምኞትህም ሆኖልሃል ከብዙ ዘመድ ወዳጆችህ ጋር ተገናኝተህ ስለደስታህም ስለሆነልህም ነገር በመፍለቅለቅ ውለህ አምሽተሃል ። ፍንጠዛህም ከል ክ አልፎ እምትጨብጠውን አሳጥቶህ የበለጠ ከም ታፈቅረው ወይም ከማንም አብልጠህ ከምትወደው ገንዘብህ ላይ ቆንጥረህ ለደስታህ መታሰቢያ ሰው ተህ ምግብና መጠጥ አዘጋጅተህ ጓደኞችህን ስታ ማታ ውለሃል ። ምክንያቱ ምን ይሆን ? ንግድህ ሆኖል ህ ብዙ ገንዘብ አግኝተሃል ሥልጣን ላይ ወጥተሃል ልጅህን ድረሃል ወይም ሚስት አግብተሃል ወይም ል ጅ ወልደሃል ልበል ። ታዲያ በእዚህ ጊዜ የምትጐነ ጨው ከአንደኛው ወገን የሚአረካውን ጣፋጭ ነው ።

ዛሬ ደግሞ እንደትላንትናው አይደለህም ሐዘ ን ተከናንበህ ትታያለህ ራስህንም ታማርራለህ ሰው ነትክንም ንቀህ ያቅበጠበጥሃል እምትናገረውንም አታውቅ ጭንቅላትህን በሁለት እጆችህ ጨብጠህ አቀርቅረሃል የትላንትናው ቡረቃህ ትዝም አይልህ በትካዜ ተጨብጠሀል በእንባም ተጨማልቀሀል ለገ ላጋይም አልመች ብለህ የመጨነቅህ ብዛት ያስጓራ ሀል ምን ሆነህ ይሆን ? ከሥልጣንህ ወርደሃል ሐብት ህ ተበዝብዟል ዘመድህን ተረድተሃል አለበለዚያም ሌላው የአንተ ቢጤ ሰው እንዲያውቅብህ እማትፈ ልገው ነገር ደርሶብህ ይሆናል ልበል ።

አሁን ደግሞ ተገድደህ የምትጐነጨው ከሌ ላው ወገን በብዛት ከሚፈልቀው የምሬት ጣዕም ነው ። ብዙዎቹም እማትፈቅዳቸው እማትመኛቸ ውና እማትወዳቸው ነገሮች ሁሉ ከእዚሁ ከመራ ራው ምንጭ ስለሚፈልቁ አብረህ ተጐንጭተሃቸዋ ልና ምሬቱ መቸም አይለይህ ። ነገር ግን ለአፍህ ማጣፈጫ አልፎ አልፎ የምትጐነጨው ያ የመጣ ፈጥ ክፍል አለና ምሬቱ ለጊዜው ያህል ይረሳህ ይሆናል ።

ይህንንም ስልህ ሰውነትህን ላስጠላህ አይደ ለም ከራስህም ከተለመደው ምኞትህና መጓጓትህ ላፈናቅልህ አልሞክርም ላድርግም ብል አልችል ምና በአንተም በሌላውም በእኔም ያለ መሆኑን ለማስገንዘብ ያህል ሞክርኩ ።

በሰው ላይ ያለ ስንቱ ሐተታ ምን ምን እንደ ሆነ ትረዳውአለህ የበለጠም ለማወቅና ለመመራ

መር ብዙ ጊዚያት እየሞከርክ እንደተውከው የማ
ይከድ ነው። ይሁን እንጅ የምታስበው ግን የሚአስ
መርርህ እጋጣሚ በደረሰብህ ጊዜ ብቻ ነው። ስሜ
ትህም በቶሎ ወደ ደስታ ስለሚለወጥ ምሬትክን
ወዲያው እረስተህ ስትበርቅ ሰውነትህ ያዘለውን
ዕድፍና ጉድፍ ያራገፍክ ይመስልሃል ይህ አውነት
አይምስልህ። ጭነቱ ምንም ባይሰማህና ባይከብድህ
አወዛውዘ የሚጥልህ የማይታይህ የራስህ ምግባር
ሸክም እንደሆነ አትዘንጋው።

ሰውነቴን ንቄው አለሁ ካልኩህ ጀምሮ ከማሕ
በራዊ ኑሮ ስለአልተለየሁ የሰውን መልካም ጥበባ
ትና ሥራዎች ማየቴና ማድነቄ አልቀረም። ብዙዎ
ችም የማደንቃቸውና የማመሰግናቸው ሥራዎች
አይቻለሁ የፈለሰሙአቸውም አርቅቀው የሠሩአቸ
ውም ሊቆች ሰዎች መሆናቸውን አልክድም ነገር
ግን ለደጋጉም ሆነ ለክፉው ሥራዎች የተደቀነው
ያው ሰው ስለሆነ እየተፈራረቀ ምድርን አስጊጠም
የቻለውን ያህል ሠርቶም ታያለህ ዳሩ ግን የሰው
ነት ጠባይ ብቻ አልሻሻል ብሎ የሠራውን ሲአፈር
ስና ያፈረሰውንም ደግሞ ሌላው ሰው ሠርቶ እንዲ
አፈርሰው ለማድረግ እየተጣጣረ አፈረሰው ፍራሽ
ሥር ተቀብሮ ይቀራል። እንደዚህም እየሆነ ትው
ልድ ሲፈራረቅ ዛሬ እኛ ያለንበትን ምድር ነገ ባለ
ተራው ይመራበታል።

እኛም ከተወሰነልን ጊዜ በላይ አንኖርምና በአ
ግራችን የሚተኩት የሚአደርጉትን አናይም። ይሁ
ን እንጅ አዲስ ነገር እንኳ ቢፈጥሩ አብዛኛውን
እኛ ስናደርገው የነበረውን አድርገው እነርሱም አ

ንደ እኛው ለሌላው በለተራ ይለቃሉ።

በየአለንበት ሥፍራ ስንኖር ጥረን ግረን እንድ
ንበላ ታገዚል ይህንንም ስናደርግ እንታያለን ግን
ድክማችንና መታከታችን ሁሉ ለምንድን ነው።?
ለማንስ ነው የድክማችንስ ፍሬ ምን ይሆን።?

የተለመደውን ሐተታ በመያዝ ድክማችን ለሀ
ገራችንና ለመጭው ትውልድ ነው የሚል ሞልቶ
ይሆናል ይህንን መናገር የሚገባው በአንድ ትው
ልድ ዘመን አብሮት ላለው ጓደኛው የሚአስብ አእ
ምሮ ያለው ሰው መሆን አለበት። እንግዲያውስ
እንደሚታየው ከሆነ ድክማችን ለየግል ፍላጐ
ታችን ሆኖ የድክማችንም ፍሬ በልቶ መሞት
ብቻ ነው።

ሞታችንም ቅጣታችን ነው እስከዚያ ድረስ ግ
ን ግምብ በሌለው ዘበኛ በማይጠበቀው ክፍት ወህ
ኒ ቤት ውስጥ ሆነን እንደልባችን እየተቀናጣን
ለምኞታችን እየተገዛን ምንም የሚደርስብን አይመ
ስለንም። ጊዜው በደረሰ ጊዜ ግን አይተነው የማና
ውቀው የብረት አጥር በዙሪያችን እንደነበረ ይከሰ
ትልናል ትልቁም የብረት በር አፈታችን ተደቅኖ
ይታያል መንጥቆ የሚአስወጣንም ዘበኛ ይገለጣል
በአጠገባችንም ይንጐራደዳል እንደከብትም ስንታ
ገድ የኖርንበት እኛ ለማዳዎቹ አውሬዎች የሰባን
ባት መሬት ተራዋን ልትበላንና ሰብታም ሌላውን
ለመመገብ አፏን ከፍታ ትቀበለናለች ከእዚህም
የሚአድነን የለም ተመልሰንም ለመምጣት አንችል
ምና የእኛ ተራ በእዚው ይወሰናል።

ትንሽም ቢሆን ደግ ነገር ሠርተን ካልተሸነን

እኛን የሚአስታውስ ምንም ምክንያት አይኖርም ። ምናልባት እንኳ ወግ ባለው መቃብር ተቀብረን መቃብራችንም በእምነበረድ አጊጦ ስማችንም በላዩ ላይ ተቀርጾ ቢታይና ቢነበብ የሚአመለክተው የስም መቃብርነቱን ነው ። አለበለዚያ ግን የትም ዋሽ ውስጥ ተወርውረን አንድ ቀን መክረኛው አጽማችንም ከአፈር ውስጥ ብቅ ብሎ ሲታይ የሰው አጥንት ተብሎ በተፈጥሮ ስማችን ብቻ ያስነሣን ይሆናል እንጅ የአገሌ አያሰኘንም ።

በላያችን ያለውን ዕዳ በሥራችንም ያለውን ክፋት አስተካክለን ከሰብነውና ከተመራመርነው ክፋና ደጉን ለመለየት የተፈጥሮ መብታችን ነው ። የሌለብን ለመምሰል ውስጥ ውስጡን ቂማችን አመርቅዞ ሳለ ላይ ላዩን ምላሳችን መሰሉን ሲሸነግል አንተፋፈርም ። ክርክራችን ሁሉ የለብንም ተንኰልም አላደረግን የማለት ሲሆን ቅንና የዋህ ሆነን ለመደማመጥ እንሞክራለን ፣ ምን ይደረግ የአንዱን ውስጣዊ ምሥጢር ሌላው እንዳያውቅበት አድርጐ እግዚአብሔር ፈጥሮታልና ነው ።

ሁላችንም እንደዚሁ ስለሆንን የክፋትና የተንኰል ወይም የሰውነታችንን እርኩስ ጠባዮች መደበቂያ ቀፎዎችን በውስጣችን ተሸክመን ደብቀን እንኖራለን ። ታዲያ መስሎን ነው እንጅ አውጥተን ብንዘረግፋቸው ብዙዎች በእዚህ የከበሩ ስለአሉ የሚወስድብን ባልነበረ ።

ይህን ሁሉ እያወቅን ወደ ስሕተት የምንነጉደው የምኞታችን ተግዥ በመሆናችንና መጓጓታችንም መጠን ስለሌለው ነው እኔ ብቻ ስለምንል

ይህም እድር ሆኖ እኛ ብቻ እንጅ ሌላ የአለ አይመስለንም ።

ሰው ፣ ሰው ፣ ሰው ፣ የማትበለጠው የማትሸነፈው የማትደመሰሰው ስምህን አክብረህ ለመኖር የምትመኘው ሐብትህን ለምን ወይም ለማን የምታከማችበትን ምክንያት የማታውቀው ለጓደኛህ ውለታ የማትሠራ ሌላው ላደረገልህ ምሥጋና የሌለህ ወገንህን ወደ ወጥመድ የምትመራ ጠባይህን ሳታርም የሌላውን ጠባይ የምትነቅፍ በወንድምህ የምትቀና በሐሰት ጐዳና የምትጓዝ ከአይንህ ጀሮህን የምታምን የሌላው ሥቃይና መከራ ደስ የሚልህ በራስህ ብቻ የምትመካ በእውቀትህ የምትራቀቅ የአሰኘኝን ሁሉ አደርጋለሁ አደርጋለሁ የምትል ሰው ሆይ መቸ ይሆን መታረሚያህ ። ?

ከንቱ ነገሮችን የፈጠረ የሰው ከንቱ ጠባይ ስለሆነ ከንቱነት እየተስፋፋ በየአንዳንዱ ሰው አንደበት ተጠራቅሞ ከአፉ እያወጣ ሲዘራው ፍሬው ወዳያውኑ እየበቀለ መኸሩም ወደ ሌላው ሰው የነገር ጐተራ ገብቶ ይከማቻል ። ከሰው ልጅም የማይለየው ጠንቀኛው የሐሰት ዘር እየበዛ ሰውን እራሱን የባሰ ወደ የሚያረክሰውና ወደ የሚአቀለው ሁኔታ ላይ ሲጥለው ይታያል ።

ሰው የሚፈልገውን ሳያውቅ እየተቅበዘበዘ በየአለበት ሲባክን የልቡን ያደረሰ ይመስለዋል ለሚሠራው ክፋትና ተንኰል የእግዚአብሔር ፍርድ ከእርሱ በላይ እንዳለና አንድ ቀንም ደምስሶት እንደሚያልፍ አይግነዘበውም ።

ሰው የአየውን ሲናገር አስተካክሎም ቢሆን

የሰማውን ሲያወራ አጋንኖ ነውና በሄዩት ለአየው እንኳ ምሥክርነቱ አጠራጣሪ ነው። ሰው ምኞቱ ለመከበር አሳቡም ለመግዘት የሚወጥነውም ተን ኩል አግባብቶ ለመግራፍ መስሎም ገብቶ ሰው የሆነውን ወገኑን ለማሳሳት ነው።

እንደተባለው ሁሉ የሰው የመጨረሻ ቅጣቱ ሞቱ ነውና የቀደማቸውን እንዳይሸታቸው ብቻ ያ፡ ሁሉ ክብሩ ተዋርዶ ጉድንድ ውስጥ ተወርውሮ በአፈር መደፈን ይሆናል።

የሰውነት ክፉ ጠባዮች ግን አብረው አይቀበሩ ምና ተለይተው ቀርተው እሌላው ላይ እየተጋቡ ሲወራረሱ ይኖራሉ የሰው ዘርም እንደዚሁ እየረ ከሰ ይዘዋወራል። የሕይወቱም ፍጻሜ በእዚሁ ዓይ ነት እንጅ ሌላ ዓይነት መጨረሻ አይኖረውም።

ጠዋት ተነስተህ ውለህ ዘረህ ስትገባ
ስትወጣ ስትወርድ ስትስቅ ስታነባ።
ኑታይ ስትሰማ መስሎህ አትበለጥ
ስታሸፍ ስትቀልድ ነገር ከፍህ ሲያመልጥ።
ከዚያም ከእዚህ ብለህ ሁሉን ስትሰበስብ
ምኞት ስትገነባ ፍላጐትህን ስትክብ።
የጉሮህን መንገድ ይዘህ ስትጐተት
ላግኝ እንጂ አልጣ ብለህ ስትሟገት።
የመጨረሻውን ቅጡንም ሳታውቀው
አለህ የምትል ሰው ከፈር የምትወድቀው።

ም ዕ ራ ፍ ፩

መቅድሙ ስለ ሀገር እንደጠቀሰው ሁሉ አንድ ሀገር ለተመራባት ሕዝብ ሰብሳቢ እናት ነች የልጅ ጅም ፍቅርና መተባበር ስለ እርሷም መኖርና መጠ ራት መታወቅና ማደግ መበልጸግና መሠራት እንዳ ትወረርም መከላከል የሕዝቧን አንድነትና ስለ እር ሷም የሚገበውን ቅናትና ኩራት ይጠይቃል።

ነገር ግን ከአንዲት ሀገር ልጆች መሀል ፍላጐታ ቸው ቅጥና ወሰን ሳይኖረው በቃኝ ሳይሉ ወይም እኔ ብቻ በማለት የሚኖሩ ከአሉ ለራሳቸው ብቻ ሳይሆን ንጹሕና የዋሕ ለሆነው ለአንዲት ሀገር ሕ ዝብ ሳጥፊያ የተቀመመ መርዘች ናቸው ማለት ይቻላል።

ሀገርስ ነፃነትስ የአንድ ሀገር ሰውነትስ ኩሮስ ሥልጣኔስ ምንድነው ያልን እንደሆነ በምንድነው ብቻ የተቆላለፈ ጥያቄ ውስጥ ገብተን እየተራዘመ ከመጄዳ በስተቀር እያወቁ እንዳላወቁ በክርክር መራቀቅ ነውና በአጭሩ ቁርጥ ባለ አነጋገር ሀገ ርም ኩሮም ሥልጣኔም ነፃነትም የአንድ ሀገር ሰው ነትም መብቱ ነው ብሎ አክብሮ ለሚይዘው ሁሉ የተሰጠው የተፈጥሮ መብቱ ነው።

ባለመብት በሆንባት ሀገራችን የበለጠ ባለመ ብት የሚአደርጉንን ነገሮች ሁሉ እንደዋዛ እየተው ናቸው ስናልፍ ወይም በመናቅ አለበለዚያም በመ ሰልቸት ስንረሳቸው ለተመራራሽ ወገኖቻችን ምን ም ሳናተርፍ ወይም ሀገራችንን በጊዜአችን ሳንጠ

ቀም በምንቸገረኝነት ብቻ የሆነ ይሁን ብለን የምን ዘነጋው ሁሉ በሆነ ይሁን ምክንያት እስከ ዛሬ የሆ ነ ሆኖ የቆየን ወደፊትም የሆነው ሆኖ ለሌላው ትውልድ ከመተላለፉ በፊት ሌላ ዓይነት የሀገር ጠንቅ ሊአፈራ እንደሚችል አስቀድሞ መገንዘብ ይገባል ።

ኢትዮጵያ ትላንትና ወይም ዛሬ የተፈጠረች የተዘረጋች ምድር አይደለችም ከአኖም በፊት የነ በሩባት ሰዎች ኖረውባት አልፈዋል ። የኢትዮጵ ያና የኢትዮጵያውያን መሠረተ ታሪክችን ከጀመረ በት ጊዜ አንስቶ በአሁኑ ትውልድ እስክ አለነው ድረስ በሀገሪቷና በሕዝቧ ላይ የደረሰውን በጥቂቱ በሕሊናችን ውስጥ ብናመላልሰው ለአለንበት ሁኔ ታ ምክንያት ሆኖ ወደኋላ ያስቀረንን በአጭር መን ገድ ልንረዳው እንችላለን ።

እነ ማን ነበሩ እነማን አሉ እነማንስ ይኖራሉ ። የተወደደችው ሀገራችን ግን ነበረች አለች የምት ኖረው ግን እንድትኖር አድርገን ስንይዛትና ስናገለ ግላት ነው እንጅ እንድትወድቅ ስናንገዳግዳት አይ ደለም ። ለዘለዓለም ትኑር ማለትም በአፋዊ አነጋገር ሣይሆን ከእኛ ከልጆቿ የሚጠበቀው የሆነ ይሁን ማለትን ትኑ ሊሆን የሚገባውን መርጠ የሚበጀ ውን ማድረግ ብቻ ነው ።

እርስ በእርሳችን በአለመስማማትና በመቀና ናት አንዱም አንዱን ጥሎ የሚመኘውን ክብር ለመያዝና ለጊዜው ብቻ በጊዜው ለመቃየት ወንድ ምና ወንድም እየተጋፉ በውስጣችን በደረሰው መጋደልና መዘራረፍ ከዘመን ወደ ዘመን እየተላ

ለፈ የኢትዮጵያ ልጆች ደም የአለ ምክንያት በከ ንቱ እየፈሰሰ ሕዝቡም እየተቀነሰ መሬቱ ተራ ቁቶ ይገኛል ።

ያለፈው አለፈ ደጉም ሆነ ክፉውም ሥራዎች ታሪክ ሆነው ስለሚገኙ በለፈው ከመጸጸትና በለፈ ነገር ላይ ከመተቸት ያለፈውን ክፉ ነገር ሁሉ የታ ረመ ትምህርት አድርገው የዛሬዎቹ ኢትዮጵያው ያን መጭውን በማመዛዘን የዛሬው ተሻሽሎ ለነገ ሊተ ካ በሚገባው ላይ መድከም ግዴታችን ነው ።

የአንድ ሀገር ዕድገትና ልማት የሕዝቧም ብል ጽግና የሚገኙት ሰላምና ዐጥቃ ሲኖር ነው ። የአ ንድ ሀገር ነፃነትም መብትም የሚጠበቀው በሕዝብ ሕብረት ነው ።

ሕብረት ሰላም ዕድገት ዐጥቃ ነፃነትም ሆኑ ብልጽግና ከተፈጥሮ እውቀትና አስተዋይነት ብቻ የሚገኙ ሣይሆኑ ከትምህርት የሚወለዱ የጥበብ ዘሮች ናቸው ። የእነኝህም የየአንዳንዱ ዘርፎች ሐተታወቻቸው ሲተነተኑ እስክ በሌለው ነገር መተ ርጐምም ሲቻል ለሰው ልጅ ዘር ማሕበራዊ ኑሮ መሠረታዊ መተዳደሪያው እነኝህ ናቸው ብየ ብል የተሳሳትኩ አይመስለኝም ።

« የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው » የተባለውን ጥቅስ ከመንን ወደ ጥበብ ጐዳና ገብተናል በምንልበት በአሁኑ ወቅት ፈሪሀ እግዚ አብሔር እንዳአድርብን ያስፈልጋል ።

ወደ ተሻሻለ ሥልጣኔ ለመግባት በተያያዝነው አመራር ቀጥለን እንሂድ ስንል መሠረታዊ የሆነ ውን የነበረንን የሀገራችን ሥልጣኔ እያሻሻልን የሚ

ነቀፈውን ባህላችንን እያረምን የሚመሰገነውንም ቅርስ አኩርተን መራመድ ይኖርብናል ።

ከሌሎቹ ከፍተኛ ሥልጣኔ ላይ ደርሰናል ከሚ ሉት አስፈላጊአችንንና ጠቃሚ የሚሆኑንብቻ መ ቀሰምና ለሀገርና ለወገን መጠቀሚያ ማራቢት ማት ረፍ ማስተማር ተገቢ ሆኖ ሣለ አንዳንድ ሳይሰለ ጥኑ ሰለጠንን ከሚሉት መሐል ሆነው የሥልጣኔ ምልክት ያልሆነውን ሥራ ሲሠሩ አይቶ ያንንም ሳያመዛዝኑ ቀድቶ ከሰለጠኑ ሰዎች የቀሰምኩት ነው ብሎ ከባሕል ውጭ የሆነ ነገር ማሳየትና ለሌ ላው ልሰልጥን በይ መግለጥ ንጹሕ ሕሊና የያዘ ውን ወገን ከማባለግ በስተቀር ትርፍ አይኖረውም እንዲያውም ከጥራዝ ነጠቅ ጥራዝ ነጠቅ ነጥቆ ጥራዝ ነጠቅ ማብዛት ይሆናል ።

ሥልጣኔ ማለት ሀገርንና ወገን መናቅና መን ቀፍ ወይም በሀገርና በወገን ማፈር አይደለም ።

ሀገሩና ወገኑ ከተጐሣቆለ ድህነት ከችግር ከጭ ንቅና ከድንቁርና ሳይነሣ አለበት ደረጃ የደረሰ የለ ም ካላባቸውም ካልተሟላ የኑሮ ደረጃ ወደ ተሻ ሻለ እድገት ለመራመድ የሚደክሙ ገና ብዙዎች አሉ ። ሀገራቸውም ገና በሙሉ ያልለማችና ያልተ ሠራች ሕዝቧም እሚገባው የኑሮ ደረጃ ላይ ያልደ ረሰ ሆኖ ሣለ የጥቂት አዋቂዎች የጥበብ ሥልጣኔአ ቸው የተራቀቀ ሆኖ ስለገፉ ለበለጠ ጥበብ ብቻ የሚሽቀዳደሙ ይገኛሉ ። እኛም ሊሆን የሚገባውን ለማድረግ ከነበርንበት ተነስተን ለሀገራችን እንሥራ ማለታችንና ጉድጉድ ማለታችን ሣይቀር በአቅማ ችንም መጠን መሥራት እንዳለብን ሳይመዘዘን በም

ኖት ብቻ ወይም ለምን እንደዚህ አይሆንም በማለ ትና ሁሉን በመንቀፍ የምናተርፈው ምኞትና ነቀ ፌታን እንጅ ደምበኛ ውጤት ያለውን ሥራ አይደ ለምና ማስተዋል እንዳይጐድለን ያስፈልጋል ።

ስለ ሀገሩ ተቆርቋሪ ያልሆነ ሰው ለሕጓ ተገዥ አይሆንም ድንጋጌዋንም የማያከብር አፉ ይዘልፋ ታል አሳልፎም ለማይገባው ዘላፊ ይሰጣታል የሀገ ሩንም ክብር በከንቱ የሚዘልፍ ሰነፍ ብቻ ነው እር ሱም የአራሱና የወገኖቹ ጠላት ሆኖ በሚነዛው መ ጥፎ ምሳሌ ብዙ ደቀ መዛሙርትን አስከትሎ የሀገ ርን ፍቅር መሠረት ለመናድ የተነሣሣ ነው ለማ ለት ይቻላል ።

የሰው ጊዜአዊ ሕይወቱ ከሀገሩ ሕይወት ጋር የተያያዘ ስለሆነ እኔ ብቻ ወይም ለእኔ ብቻ በማ ለት በማታለል በማጭበርበር በመደለልና ወገንን ሀገርን በሚጐዳ ነገር በመስማማት ሀገርንና የሀገ ርን ክብር በሚአዋርድ ጉርሻና ጉበ መሸነፍ ወይ ም ወገንን በሐሰት ወንጅሎ ዋጋ ለመቀበል መን ገት አርቆ አለመመልከትና ደደብነት እንደሆነ ጥር ጥር የለውም ።

ሀገርና ወገን ማለት የተወለዱበት ቀበሌና የተ ወለዱት ዘመድ አዝማድ ብቻ ሣይሆን በጠቅላ ላው አንዲቷን ሀገርና የሕዝቧን አንድነት የሚ ገልጽ ነው ።

ኢትዮጵያ የእራሷ የሆነ ሥልጣኔ የግሏም የሆ ነ የጨዋ ባህል ይዛ የኖረችና አሁንም በዘመኑ ሥልጣኔ ለመግፋት የምትጣጣር ሀገራችን ናት ። ሕዝቧም የጨዋነት ቅርሱንና መተዳደሪያዬ ብሎ

ይዘት የቆየውን ባሕሉን ልማድ አድርጐ ቢይዘ ውም ከባሕሎቹና ልማዶቹ መሀል ሊነቀፉ የማይ ችሉ ለሌሎቹም እንኳ ምሣሌ ሆነው ሊጠቀሱና ሊያዙ የሚገባቸው ብዙ ደጋግ ነገሮች እንዳሉ ማ መን ያስፈልጋል ።

በእዚህም ዓይነት መሻሻልን እያረሙና እየታ ረሙ ለመሄድ ሲቻልና ይህንንም ለማድረግ ጊዜ ሲጠይቅ ከጊዜው በፊት ሆነን እንገኝ ብሎ መዘበረ ቅና ማዘበራረቅ ሀገርን ወደ ባሰ ጉዳት መምራት እንደሆነ መገንዘብ ይኖርብናል ።

የሀገሩን እድገትና ሥልጣኔ የሕዝቡንም ደህን ነትና ስለ ከፍተኛ ኑሮው ደረጃ ማደግ የማይመ ኝና የማያስብ በአሁኑ ጊዜ የለለ አይመስለኝም ነገ ር ግን አንዳንድ በጐ አሣቢና ሁሉን ያወቅን ነን በሮች ሌላውን ወገን ያላወቀና ያልገበው ተመቅ ኝና ልዩ አሳብ ያለው እንዲያውም የሀገሩ እድ ገት እንቅፋት ነው በማለት በሚኣትቱት አሉባልታ የሚነዛው ዕድፍ እገበውም አልገበውም ላይ ማረፉ ስለማይቀር ለማንኛውም ወገን ሊበጀው አይችልም የእዚህም አይነት ሽሙጥና ማንኛውም አይነት እን ጋገር ሁሉ ለሀገሪቷ ፈውስ የሚሰጥ መድኃኒት አይሆንም ።

ጥንታዊቷንም የዛሬይቷንም ኢትዮጵያችንን የ ወደፊትም እንድትሆን ካስፈለገ በቅን መንፈስ በፍ ቅርና በመተባበር ደግፈን እናዘልቃታለን ብለን ካል ተነሣን በቀር በአሉባልታና በመነቃቀፍ በሐሰት በ መነዳትና በወሬ በመሰልጠን በንጹሑና በተባረከው ም ሕዝቧ ተንኰል በመዝራት፣ እንደዚሁም በሰው

ሀገር ጉዳይ ውስጥ እየገቡ አሳቢ በመምሰል የሕዝ ቧን መነጣጠል ለሚገፋፉ ባዕዶች ደጋፊና ተባባሪ ሆኖ በመገኘት ጥቅም ይገኛል ብሎ የሚአስብ ቢኖ ር በተሳሳተ መንገድ መሄዱን ይረዳው ። ከእንደዚህ ያለም ሰበኪያን መራቅ የማንኛውም ሀገሬን እወዳ ለሁ የሚል ሰው ጥንቃቄ መሆን አለበት ።

ለአንዲት ሀገር ከልጆቿ የበለጠ አሳቢና ደጋ ፊ ሊኖራት አይችልም ። አሳቢ መስለው ልጆቿን በመለያየት የሚጠቀሙ እነማን እንደሆኑና የመለያ የት ትርፋም ምን እንሆደነ ሀገራቸውን ወዳድ የ ሆኑ ሰዎች ሁሉ አእምሮ በቀላሉ ሊመዝነው ይችላል ።

የራሳቸውን መስፋፋትና ወይም የራሳቸውን ጥቅም በሰው ሀገር ላይ ለመዘርጋት በሰው ሀገርና በሕዝቧም መለያየት መጠቀም የሚፈልጉ ሁሉ ጠ ቃሚ መስለው ውስጥ ውስጡን ሲመርዙ ሕዝቡም መንግሥቱን እንዲጠላ ሲገፋፉ ያልሆነ ሐሰት ሲሰ ብኩ የእነርሱ አዳናቂ ሆኖ አብሮ መጨፈር ከለ ማመዛዘን የተነሣ የበዕድ መሣሪያነትን መምረጥ ይባላል ።

የሥልጣኔ መሪዎች የሆኑ ወይም ነን የሚሉ ስለሀ ገራችን አለመሰልጠንና ስለ ሕዝቧም አለመማር ሲወቅሱንና በየጊዜውም በየምክንያቱ ሲዘልፋን ሲአሳጡንና ሲወነጅሉን ይገኛሉ፤ ተችሎን ቢሆን ኖሮ እነርሱ እደረሱበት ለመድረስ ለዘመናዊ ሥል ጣኔስ መቸ ዋጋ ሳንሰጠው እንቀር ነበር? ጨቋኖስ ለእዚህ ያደረሰን ማን ነው? ጊዜ ሠርቶብን ከሚሰ ለጥነው ዓለም ተለይተን በብዙ ምክንያቶች መን

ገድ ተዘግቶብን በእዚህም ላይ ደግሞ አፍሪካን ለመከፈል እንደዚሁም የሥልጣኔ ደረጃቸው ደከም ብሎ የታዩትን አህጉሮች ለመውረርና ለመግዛት ብዙዎች ሠለጠንን የሚሉት በጊዜው የነበሩት ይሻ ሙና ይሽቀዳደሙ ስለነበር ኢትዮጵያ የመጨረ ሻው ጉርሻ እንድትሆን ዙሪያዋን እያከበቡ አፍነው ስለ አቆዩአት ከሌላው ከሠለጠነው ዓለም ተለይታ የራሷ በሆነው የሥልጣኔ ቀርስ ስትታገል ቆየች ። ወሰኗንም እያሰፋ ሊናጠቁዋት መጥተው የነበሩትን በተቻላትና በነበራት አቅም ስትተናነቅ እንደነበረ እርግጥ ነው ።

ናፒር በኢትዮጵያ ላይ በዘመተ ጊዜ ያንን ያ ህል መሰናዶና ድርጅት ተደርጐለት ሲመጣ አጼ ቴዎድሮስ የአሰሩዋቸውን የውጭ ዜጐች አስፈ ትቶ ለመሄድ ብቻ ኖሩዋልን? ወይስ ሀገሪቷንም ለመውረር ታገዘ ኖሮ ይሆን ።? የእዚህን ትክክለኛ መልስ ለመስጠት ይችሉ የነበሩት የናፒርን ጦር ከፍ በለ ከሣራ ከያለበት አግዘው ያሠማሩ በላጊዜ ዎች አሁን የሉምና መመራመር ያሻ አይመስለ ኝም ። በየታሪኩ መጽሐፍ ላይ እንደተተቸው ግን የናፒር ዘመቻ በኢትዮጵያ ላይ ሳይሆን በአጼ ቴዎ ድሮስ ላይ ብቻ የተሠነዘረ መሆኑ ተገልጿል ይህ ም የተደረገበት ምክንያት ቆንሲልና ሌሎች የው ጭ ሀገር ዜጐች አለአገባብ በመታሠራቸው በኋ ላም የታሠሩትን ለማስፈታት መልክተኛ ሆኖ የተላ ከውም በተጨማሪ በመታሠሩ የታሠሩትን ለማስፈ ታትና ለመመለስ ነበር ተብሏል ። እርግጥ ሊሆን ይችል ነበር ምክንያቱም ትልቋ ብሪታንያ የገነነች

መንግሥት እንደነበረችና አሁንም እንደሆነች ሁሉ በዜጐቿ መታሠር ምክንያት የትልቅነቷ ክብር የተ ነካ መስሎ ቢታያትም ለሁለት ዜጐቿ ስትል ብቻ ያንን ያህል ከሣራ ያስወጣ ጦር አዘጋጅታ ላከች ብየ አልገምትም ። ይህንንም ለምሣሌ ያህል ለመጥ ቀስ እንጅ ለወቀሳ ወይም ታሪክ ለመጻፍ ስላአልተ ነሣሁ ከእዚህ በላይ ለመዘርዘር አልመኝም ። እንዲ ያውም ለእንግሊዝ ሕዝብ ያለኝ ከፍተኛ አስተያየ ትና አድናቆት እጅግ የላቀ ነው ፤ ስለ ኢትዮጵያም ነፃነት በተደረገው ተጋድሎ ስለ እኛ የተሰውትን የጀግኖች ደም አልዘነጋውም በበኩሌም የማደረሰ ውለታ አድርጌውለሁ የሀገሬም ሰዎች በእዚሁ እንደሚተባበሩ እመኛለሁ ።

እንደዚሁም የአድዋን ጦርነት እናስበው ለመ ውረር በታቀደ አሳብ የተነሣ አልነበረምን በጊዜ ውስ አፍረው የተመለሱት ጠላቶቻችን ወዳጆው ተወዳጅተው የወዳጅ ጠላት ሆነው እንደገና ሀገራ ችንን ወረዋት አልነበረምን ፤ በወረራቸውስ አጭር ጊዜ ውስጥ የግፍ ደም በማፍሰስ ወገኖቻችንን በክ ንቱ በመጨፍጨፍ የተረፈውንም ከራሳችን ምድር ገጽ ላይ ለመፋቅ ያደርጉት የነበረው የግፍ ድር ብና ይሰሩበትስ የበነረው የፈረ መሣሪያ አይታ ወሰንምን ።?

«ከእናት ትሻል ሞግዚት» እንደተባለው ስለ አራሳችን ጥቅምም ሆነ በደል ከእኛው ከራሳችን የበለጠ አሳቢና ተቆርቋሪ እንደሌለን አውቀን የነ ገረ ሪሪዎችን ምላስ በማዳመጥ ሁላችንንም ወደ ጥፋት ከሚመራን ተንኰል ለመሸሽ ንቁዎች ሆነን

መገኘት አለብን፤ በልቃመነም ተስፋ አንጠመድ።

ከሁሉ የባሰ አንድ ሀገርንና ሕዝቧንም ወደ ከንቱ ምሣሌ የሚመራው ያልቃመነ ተስፋ ነው። ውሸን፡— «ሙዳ ሙዳ ሥጋ ተቆራርጦ የተበተነበት የወተት ባሕር አለ» ቢሉት የትኔው ሣይል ጅው ብሎ አሮጠ ይባላል። ስለ ምሳሌው ይቅርታ እየለመንኩ ያልቃመነ ተስፋን ከእዚህ አይነት ምሣሌዎች ጋር አመሳስለው አለሁ።

ያሳለፍነውን ችግርና ጭቆና ጥሰን የሥልጣኔን ጣዕም ለመሳተፍ ወደ ሌላው ምዕራፍ በተዛወርን በት በአሁኑ ጊዜ መተባበርና ለሥራም መሽቀዳደም እንዳለብን ሳይታወሳ በጠላት ተወርረን ብዙ ጊዜ ቆይተን ቢሆን ኑሮ ይህን ጊዜ አተሻለ ሥልጣኔ ደረጃ ላይ በደረስን ነበር የሚሉ በዕድሜ ሰውሠርቶ ይጠቅማቸው የመሰላቸው አንዳንድ ሰነፎች ሲተቹ ሰምቼአለሁ። ግን ከፍ ያለ ስሕተት መሆኑን ሊረዱት ይገባል ምክንያቱም የኖረ የከፍተኛ ሥልጣኔ ርዝራዥ ከነበራቸው አንዳንድ አህጉሮች በስተቀር በባዕድ ተወርረው በቅኝ ተይዘው ሲገዙ ከነበሩት አህጉሮች ከኢትዮጵያ የበለጡት የትኞቹ ናቸው ?

ከተማወቻቸውን ያደመቋቸው ሕንፃዎች፤ መሬቶቻቸውን ያስጌጡአቸው ተክሎች፤ ሰብሎቻቸውን የሚዘረግፉት እርሻዎች፤ ማዕድኖችን የሚተፉት አዘቅቶች፤ ልዩ ልዩ ሸቀጦችን የሚሠሩት ፋብሪካዎች ሌሎቹም እነዚህን የመሳሰሉት ሁሉ የእነማን ይሆኑ ?

ይህንንም ስጠቅስ ሌሎቹን ወገኖቻችንን ለማሸ

ሚጠጥ ሣይሆን ባለፈውም ሆነ በአሁኑ ለወደፊቱም አንድ አይነት ችግር እንደነባረብን እንዳለብንና እንደሚኖርብንም ለማስገንዘብ ያህል ብቻ ነው።

ዛሬም ቢሆን ዓለም ወደ መግባባትና መቀራረብ ላይ ደርሷል ወይም ሞክሯል በሚባልበት ወቅት ብዙም በቅኝ ተይዘው የነበሩ አህጉሮች ነፃ እየወጡ በጄዱበት ጊዜ ነፃም ወጥተዋል ተብሎ ራሳቸውን ለማስተዳደርና ሃገራቸውንም ወደ ተሻሻለ የሥልጣኔ እርምጃ ለመምራት በሚጥሩበት ሰዓት ጣልቃ ገብ የሚሆኑትን አንዳንድ አስቸጋሪ ጠንቆች የሚፈጥሩባቸውና የሚፈጥሩብን ሰብአዊ ዕድገታችንን የማይወዱት መሆናቸው አያጠራጥርም።

ዘመኑ አስገድዶ ሁሉም የነፃነት ፋና ይዞ ጥበብን ሲፈልግ የሚአጋጥሙት ችግሮች ብዙዎች ናቸው፤ ጥበብና ሥልጣኔም የሚመጡትና በሀገራችን ሊደረጁ የሚችሉት ከወዲያ ነው ብለን ካመንን ዘንዳ አሁንም ወደዚያው ማስተዋላችን አይቀርምና ለትክክለኛው እርምጃችን ቅሰማሥትና መማባት ያስፈልገናል። ዘመን ተለውጧል ዘመንም ይተካል የተለወጠውም ዘመን የተለወጠ ነገር አሳይቷል የሚለወጠው ዘመን ደግሞ የሚያስከትለውን ለውጥ አናውቅምና ወቃሽቻችንን ብቻ ሣይሆን አንኩብኳቢዎቻችንንም ማዳመጥ ግዴታችን እና ድርገው።

የምንሸምተው የሥልጣኔ ቅርስ ከጀአግራፊ አቀማመጣችን በወጣ ወይም በራቀ ገበያ ስለሆነ ለምንፈልጋቸው ጥበቦችና ሸቀጦች ፍላጐታችን አሰገድዶን የምንሸውን ሁሉ ለመቅሰምና ለማግ

ኜት የምናደርገው መጣጣር ፖለቲክ ውስጥ ገብተን እንድንታሽ አድርጐናል። ይህም የዓለም ሕዝብ ማሕበራዊ ኑሮ የሚጠይቀው ነገር ስለሆነ ከእዚህ ሽንጐ መውጣት አይቻልም።

ፖለቲክ ማለትም አንድ ራሱን የቻለ የጠቅላላው አነጋገር ትርጉም ቢኖረውም አንዳንድ ቅርን ጫፍ ትርጉም የሠጉትን በአውሩ ስገልጣቸው ፖለቲክም ማለት የግርግር የሽብርና የነገር መገበያያ አለበላዚያም የአራስን ጥቅም ለማደርጀት በብሩህ አእምሮ በስል መላ የሚተቹበት ወይም ተሸረዳ ያው የሚወዳጁበት ክልተግባቡም የሚለያዩበት በአንድ በኩል ለማሕበራዊ ኑሮ የሚአገለግል መሣሪያ ሲሆን በሌላው በኩል ደግሞ እርስ በእርስ ለመተዳደር የሚበጅ የሚከተሉትንም መንገድ አሥምሮ የሚያስይዝ ዘዴ ነው። በሌሎችም ብዙ መንገዶች ስለሚፍታታ በእዘህ መነታረክ እንዳይሆን የተገለጠውን አጭር ምሳሌ አጠቃልዬ ፖለቲክ ማለት ለክፉም ሆነ ለደግ ነገር የሚውል ጠንካራም ደካማም ሆኖ እንደያዙት አይነት ለጠቀመበት ወይም ሊጐዱበት የሚአስችል የጦልዘ መሣሪያ ነው። በምንይዘው ፖለቲክ ወዳጅም ጠላትም ማፍራታችን የማያጠራጥርነውና ክልኩ አልፎ እስቲደፈርስ ድረስ ጠላትንም እንደ ወዳጅ ማየት ፖለቲክ ይባላል።

የሚዐጀንን የውጭ ፖለቲክ ከመከተላችን በፊት የሚበጀንን የውስጥ ፖለቲካችንን ማደራጀት የሚገባን እኛው ነን። የውስጥ ፖለቲካው ያልደረጀ ሕዝብ ብዙውን ጊዜ ሊከተለው የሚገባውን

የሌላውን ሀገር ፖለቲካ አጥርቶ ሊያውቅና ሊጠቀምበት አይችልም። የአባቶች ምሳሌ «የቆጡን አወርድ ብላ የብብቷን ጣለች» ይላል።

በአላንበት ትርምስና ንትርክ ውስጥ ገበያው ደርቶ ያም ያም ልዩ ልዩ ትችቶችና ልዩ ልዩ አሳቦች ማሰማት ወድዶ ወይም አለይበሉኝ ለማለትና ሁሉንም መስሎ ለመገኘት ነገር ሲያማቱና ሲያዘበራርቁ መገኘት ማሰማትና መታየት ያለውን እስከማጣት ያደርስ እንደሆነ እንጅ የሚአሻሽል ነገር ይኖራል ብሎ መገመት አየስችልም።

እንግዲያውስ የውስጥ ፖለቲካችንን መሠረት እናጥብቀው ያልን እንደሆነ ከሁሉ በፊት ልናውቀው የሚገባን ወደየት ወደምን እንደምንመራ አጥርቶ መገንዘብ ይሆናል፡ ይኸውም ሲነገር እንደቆየው ወደ ሥልጣኔ ወደ መሻሻል መመራታችን የማይከድ ነውና ማነኛቸውንም ለእዚህ ጉዳይ የሚአገለግሉንን መሣሪያዎች በመልክ በመልኩ ማደራጀትና ማደርጀትም ይኖርብናል።

በአንዳንድ ነገሮች እረቀንና ተራቅቀን ስንገኝ በአንዳንድ ነገሮች ደግሞ እነበርንበት ሆነን ስንል ኩሰኩስ እንታያለን ይህ ከሁለት አይነቶች አሠራር የተቀሰመ በመሆኑ ምክንያት ሊሆን ይችል ይሆናል። ከእዚህም ሌላ ሁለት አይነት አድሮች ስለአሉም ነው፡ በለጥ ያለው የአድር ወገንና አነስተኛው የአድር ወገን ለሁለት ተከፋፍለው ስለሚገኙ አነስተኛውም የአድር ወገን ካለመብዛቱ የተነሣ ተሰሚ ድምጽ ስለማያገኝና ቢጮህም ስለማይሰማ ምንም ማድረግ ባለመቻሉ የምንቸገረኝና የምንአለ

ብኝ ቆስቋሽ ሆኖ ውስጥ ውስጡን አሳቱን ያቀጣጥ ላል። አብዛኛው የአድር ወገን ደግሞ ያለውን ልማ ድና የራሱን ባሕል ቀርስ እያቆሻበለ መኖር ስለሚ ፈልግ በመሰለውም አይነት አምኖ ስለሚመራ ወደ ፊት ምን እንደሚጠብቀው እንኳ ቢረዳው የጊዜ ውን ሁኔታ ላለመለወጥ ሳይመኝ የቀረ አይደለምና ያለበትን ኑሮ ይወደው ይሆናል።

ዘሮ ዘሮ ጥቅሙን የሚጠላ ስለሌለ መሠረትን በሚያፈርስ ድርቅ በለ ለውጥ ተለወጥ ብሎ ያል ተረዳውን በግድ አሳምናለሁ ብሎ ከመነሣት በለሰ ለሰ ምላሌ ማስረዳት የሀገሪቷን ጥቅም፤ እድገትና የሕዝቧንም መተባበር የመጀመሪያ ቅድሚያ ስለሚ ሰጠው የውስጥ ፖለቲካችንን የሚያጠነክረው ዋና መነሻ ሁለቱን እድሮች አስተባብሮና አስታርቆ እን ዲግባቡም አድርጐ መምራቱ መሆኑን ተረድቶ ወደ ሌላው ሥራ ማለፍ ነው፤ ይህም ትልቅ መዳኛና ፈውስ ለመሆኑ አያጠራጥርም።

እንግዲህ የውስጥ ፖለቲካችንን ለማደራጀትና ለማደርጀት ስንመኝ እነኝህ ሁለት እድሮች እነማ ንና እንዴት እንደሆኑ በቀላሉና በአጭሩ ልንረዳ ቸው ይገባናል።

እንደሚታወቀው ሁሉ ሁለት ክፍሎች አሉ፤ እነዚህም የተማረውና የመሀይም ክፍሎች ሲሆኑ፤ ቀደምኩ የሚለው የተማረው ክፍል መቅደሙን ለ ራሱ ብቻ ሳያደረገው ላልደረሰውም መሀይም እን ዴት አድርጐ ሊደርስ እንደሚችል መሪ በመሆኑ እንኳንስ አሠራሩና አመራሩ ቀርቶ አነጋገሩ እንኳ ቢሆን የተመዘነና ትሕትና የለበሰ እስትንፋስ ሆኖ

ደግ ሥራን፤ ደግ ምኞትን፤ የታረመም ምክርን የ ሚሰጥ ቃል መሆን ይገባዋል እንጅ፤ አንዳንድ አሳ ሳቾች የመሀይም ወገን የተበለው የሚበሳጭበትን ተበሳጭቶም ለማንም ሊጠቅም የማይችል ጉድለት እንዲያደርግ መገፋፋት ትልቅ ስሕተት ነው። ሰው ን በተቻለ መጥቀምና የሚጠቀምበትንም ዘዴ ማስ ተማር ካልሆነ በቀር በሰው መጠቀም ወይም እጠ ቀማለሁ ብሎ ሰውን ወደ አላሰበበት ተንኰል መ ምራት፤ የተፈጥሮ መብቱ ጓደኛ ያደረገውን አካል በብልጠት ከበለጥኩት ብሎ መናቅ ማለት ነው። ሰው ወይም ሕዝብ መጫወቻና ለግል ጥቅም ማዳ በሪያ ለሥምም ማስጠሪያ መሣሪያ መሆን የለበትም፤ ሕዝብን ማወናበድና ከመስመሩ እንዲወጣ አድርጐ ተንኰል ማስተማር ወደ ክፉም መምራትና መገፋ ፋት የሀገርና የሕዝብ ጠላትነት ነው። ሕዝብ ስለ ሀገሩ እንጅ እራሳቸው ላበጠ ጉጉዎች መስዋዕት መሆን የለበትም።

ሁልጊዜ ሕዝብ ማመሃኛ ሆኖ ስለ ሕዝብም እ የተባለ በሚነገረውና በሚሠራው ምንም ዓይነት የ ሕዝብ ጥቅም አለመሠራቱን የአሁኑ ጊዜ የበለጠ አሳይቷል። ይሁን እንጅ የቀድሞው ጊዜ ስለ ሕዝብ ማሰብ ግን ብዙ ለውጥንና ብዙም የሕዝብን እድገ ት አሻሽሎ ቢገኝም በእዚህ ዓላማ ተነሣሥተው የነበሩት ጥንታውያን መሪዎች ስለ ሕዝብ ያሻሻሉ ት ነገር ኖሮ ተጠቅመውበትም ሀገራቸውንና ሕዝባ ቸውን ጠቅመው አደርጅተውት ስለአለፉ፤ ወደ ከ ፍተኛም የኑሮ ደረጃ የአደረሱት ሕዝባቸው ተወ ራርሶ እተሻሻለ ኑሮ ላይ ስለደረሰ ጥቅሙን የጋራ

አድርጉ በመተባበር ሲኖር ይታያል። ስለእዚህም ክፉውን ትቶ ደጉን ብቻ አይቶ በቅን ተመርቶና መርቶ የሚገባውን እየቀዱ በማድረግ ፋንታ፤ ዘመን አመጣሽና ብርቅ የሆነባቸው አንዳንድ ሰዎች ግን፤ በማገለባበጥና በሕዝብ በማሳበብ በሕዝብም ደም በመጫወት ሥልጣን ላይ ለመውጣት የሚያደርጉት ሙከራ ሁሉ በሕዝብ አጋዥነት ወይም ደጋፊአቸው በሆነውም ባልሆነው ኃይል እየሆነ ሥልጣን ከ ጨበጡ በኋላ ሕዝብን ከመጨቆን በስተቀር ስለ ሕዝብ የሚያደርጉት ነገር የለም። ምናልባትም ወደ ኋላ የቀረውን ሀገርና ሕዝብን በመጨቆንና በጥብቅ ሥነ ሥርዓት ይዘ፤ ወደ ከፍተኛ የኑሮ ደረጃ ለማ ድረስ ይቻላል ብለው እንኳ፤ የገመቱና በእዚህም መንፈስ ሠርተው ከጊዜ ብዛት እናሻሽለዋለን የማ ለት አቅድ ኖሯቸው የሞከሩ ቢኖሩም ሕዝባቸው ተጨቁኖ መድረሻ እስኪያጣ ድረስ ሆኖ ነው፤ ሌላ ዓይነት ለውጥ ወይም ከጥቂት ጊዜም በኋላ የእነርሱ ቢጤው ሌላው ባለአዲወሎሺ ሲነሣ ደግሞ ሥራቸውን ሲያገላብጠው ይገኛል። ይህም በዘ ያው መንፈስ የተነሣሣ ሲሆን አሁንም ያው የቀድሞውን ጨቋኝ የደገፈው ሕዝብና ኃይል ይህንንም የሚያደ ርግ መሆኑ አያጠራጥርም። እንግዲህ የሕዝብ ጥቅ ም የትኛው ላይ ይሆን? ሕዝብስ ስለራሱ ጥፋት ለምን ይሰለፋል? በመገለባበጥ የአንድ ሀገርና የሕዝ ቧስ እድገት እንዴት ሆኖ ሊመጣ ይችል ይሆን? በእዚህ ጉዳይ ጠቃሚና ተገቢ ነው ብሎ የሚከራ ከር እንደማይጠፋ አምናለሁ። ነገር ግን በበኩሌ ስለ እማላምንበት አልደግፈውም። እንደዚህ ያለ

ውም ብልግና በሀገራችን ቢለመድ ጥፋትን እንጅ ልማትን እንደማያስከትል መረዳት ያስፈልገናል። ስለዚህም ከእንደዚህ ያለው ስሕተት እርቆ መተባ በርንና ተገላልጦ መነጋገርን፤ መመካከርን፤ መወያ የትንና መግባባትን ተመርኩዞ መሥራት የበለጠ ውጤት መስጠቱን በማመን መራመድ ይኖርብናል።

ም ዕ ራ ፍ ፪

የፖለቲካ ተቃዋሚ ወገን የሌለው መንግሥ ት ሥራው አይሠምርለትም፤ ቢሠምርለትም ከመ ወቀስና ከሕዝብ ማልጐምጐም አይድንም፤ እንዲ ያውም ወደ መዋለልም፤ ወደ መንገድገድም ያደ ርሰዋል። ብዙ የፖሌቲካ ወገን ያላቸውም አህጉሮች ሲተራመሱ ይታያሉ፤ ይህም ጥሩ አይደለም። አንድ የፖሌቲካ ወገን የሚከተሉ አህጉሮች ደግሞ ሳይ ዝናኑ ይኖራሉ፤ ይህም ተገቢ አይደለም። ምንም የየአንዳንዱ የፖሌቲካ መሪ ልዑን ባይ አሳብ የተለ ያየ ሆኖ ተገኝቶ ሁሉም በየበኩሉ እኔ እኔ ሲል የሀገርንና የሕዝብን ኑሮ ሲያመሳቅል ከመገኘት እን ደምንም ተዋህዶና ተግባብቶ ሁለት የፖሌቲካ ወገ ን ክፍሎች ብቻ መኖርና መደርጀት ለአንድ ሀገር እድገትና ስለ ሕዝቡም መልካም አመራር በቂ ይ መስለኛል፤ ይህም አዲስ ነገር ሳይሆን ተደርጐ የታ ዬነውና ልዩ ማስረጃ አያሻውም።

ተግባብቶም በእዚህ ላይ መሠረት ለመጣል መ ቻል ትልቅ ዕድል ነው፤ ይህም መሆን አለበት። አሠ

ራሱ ቅጥና ወግ እንዲኖረው እንዲሠምርና እንዲለመድ ሆኖ ከተያዘ ፍሬው ወዲያው እንኳ ባይገኝ መሸጋገሪያ ሆኖ ከተዘረጋ በኋላ ጠቃሚነቱ እያደረ እንደሚገለጥ ስለማያጠራጥር ወደ እምንፈልገው ግብ በቀላሉ አስተካክሎ ሊመራንና ሊአስተባብረን ይችላል።

ሰው በራሱ ከተመካና ስለ እራሱ ብቻ ከሰበከሰው ጋር ሊኖር አይችልም። የእራሱን አሳብ ብቻ ተርጓሚና እኔ ያልኩት ብቻ ይሁን የሚል ከሆነም የማኅበራዊ ዕድገት አይስፋፋም። ስለዚህም ማንኛውንም ሁሉ የጋራ ጉዳይ በማድረግ ተመልከቶ አጣርቶና ተባብሮ ለሚበጀው ነገር ብቻ መጠመድ ፍቅርን ስለሚጠይቅ አንተ ትብስ፤ አንተ ትብስ፤ ተባብሎ መፎካከር ቅን መንገድን ያመራልና በእዚህ ዓይነት መጓዝ ግዴታ ነው።

የሚመሰገኑና የሚነቀፉ ባሕሎቻችንን ለይተን አውቀን የምንተወውን ትተን የምንይዘውን ማዳበር አለብን። በየጐራው፤ በየሸንተረሩ፤ በየመንደሩና በየጐጡ በየጐሣውና በየክፍሉ በየሃይማኖቱ፤ ከመመካት ለአንዲት ኢትዮጵያ ብለን የምንሠራው ሁሉ የጠቅላላው መደርጃ ጥቅም መሆኑን ብቻ እንመንበትና እንነሣ።

ሥልጣን የሌለው ሥልጣን በያዘው አይመቅኝ፤ ያልተገባም ሐሜትና አሽሙር ዘለፋም አያድርግበት፤ «ከበሮ በሰው እጅ ያምር ሲይዙት ያደናግር» እንደተባለው ይሆናልና እንደዚሁም አንዱ ከሥልጣን ሲወርድ የሚተካው ባለሥልጣን ትጋቱንና የአሠራሩን ቅልጥፍና ያሳይ።

ከአዳማጭ የሚፈጠሩትና የሚፈልቁት ወንድ

ምና ወንድም ማለያያዎች ሕዝብና መንግሥትን አጣይዎች የሆኑ የአለአዋቂ ስሕተቶችና አሉባልታዎች ሁሉ ጎብረትን የሚያጠፉ መሆናቸውን መገንዘብና የወሬ ንግድን ማስቀረት ያስፈልጋል። ይሁን እንጅ ሀገርን የሚያጠፋ የሕዝብን ክብር የሚያጓድል ነገር እሚደርስ ቢሆንና ሳይታወቅም ሊደርስ እንዳይችል የተረዳ የሰማ ቢኖር አስቀድሞ መግለጥ ማንኛውም ሀገሩን የሚወድ ንጹሕ ኢትዮጵያዊ ሁሉ ሊያደርገው የሚገባ ይሁን።

ሕግ እንዲከበርና እንዲጸና አዋጅም እንዲሠራ አድልዎና ልዩ አስተያየት የሚባሉት ይፋቁ፤ ሥልጣንም ማዕርግም ለግል ጥቅምና መከበሪያ አይሁን፤ ማንኛውም የሀገር ሰው በችሎታውና በሥራው ብቻ ይመረጥ እንጅ በወገንና በባለወገንነት አይደገፍ። በጥፋት የተገኘ ባለሥልጣንም ሆነ ተራ ሠራተኛ በሚገባ ተመርምሮ ከተፈረደበት ወይም ከተቀጣ በኋላ ተመልሶ ሥራ እንዳይዝ እንዲያውም ስለ ጥፋቱ ለሕዝብ ተገልጦ ይነገርበት።

አንዱ በአንዱ አላፊነትና ሥራ ውስጥ አይግባ፤ ሥነ ሥርዓትም ይኑር፤ ከሕግ ውጭ ይደረግልን ለሚል ሁሉ ያለሥጋትና ትልቅ ትንሽ ሳይባል አይቻልም ይባለው።

ከመንግሥቱ ገቢ አብዛኛው ለትምህርትና ለልማት ለጤና ጥበቃ እንዲውል ይደረግ፤ ሕዝቡ ራሱ የየክፍሉን ፀጥታ እንዲያከብርና እንዲያስከብር በየጊዜው ይነገረው፤ ይመከር። የበለጠ ወደኋላ የቀረን ሕዝብ ማሠልጠኛ ዘዴ ማሳየት ብቻ ስለሆነ ማንኛውንም ሁሉ ለማሳየትና ለመምራት የሚያስችሉትን

መሣሪያዎች እናብዛ ቅንነትም እንጨምርበት ።

የኢትዮጵያ መሬቶች መሐል ሀገሮች ብቻ አ ለመሆናቸውን ተረድቶ እነዚያ ላይ ብቻ ከመራኰት ሌሎችም ክፍሎች የሚለሙበትንና የሚሠሩበትን ድርጅት ማድረግ አስፈላጊ ይሁን ።

ወጣቶች ወንድሞቻችንና ትጉኃን ተማሪዎቻ ችን ቅጥ ይኑራቸው ፤ በአስተያየት ብቻ በአንድ ሌ ሊት ወደ እሚመጡት ግብ ተለውጦ ማደር አለመ ቻሉንና በልዩ ልዩ አሳብም የኢትዮጵያ ዕድገት ችግር የሚከናወን አለመሆኑን ይረዱትና እርዳታቸ ውም ተምሮ ማስተማር ይሁን ።

ጽኑ መንፈስ ፤ ትክክለኛ ለሕግ ተገዥነትና የጋ ራ ጉዳይ ብሎ መሥራት በአሳባችን ይደር ።

የምናየው ሁሉ አያስቀናን ፤ ደህነታችንንም ነ ውር አድርገን ሳንቆጥረው ለመሻሻል ብቻ እንተባ በር ፤ ሲሆን ካለመሥራት በስተቀር ድህነት እንደ ሌለብን እንረዳው ፤ የባሱ ደህ የሆኑ አህጉሮች ያል ሠለጠኑና ወደኋላ የቀሩ ክፍሎች እንዳሉ እንመን ፤ እነማን እንደሆኑ እዚህ ላይ መዘርዘር ባያሻም እግ ር አድርሷቸው የተመለከቱት ሁሉ ራሳቸው ይፍ ረዱት ። መንፈሳችንን ዝቅ አድርጐ ለማሳየትና ለ ምቀኝነት ሲሉ አጐሣቁለው ወይም አክፋፍተው የሚአሳጡንን አስተያየት ተከትሎ እራሱን የሚጠራ ጠር አይኑር ፤ — በዚህም የተነሣ የመንፈስ ዝቅተ ኛነት አይደርብን ።

እራሳችንን ቀና አድርገን ወደፊታችን ከተመለ ከትን የማንደርስበት ነገር የለም ፤ የሰው ዘር እንኳ ንስ በመፈጠር በአስተያየትና በአእምሮም አይበላለ

ጥም ፤ ነገር ግን አእምሮውን እንዲታነጽ ሳያደርግና በራሱ ግል ጠባይ እራሱን ከሚያስነቀፈው ነገር ባ ለመራቁ ከሌላው መሰሉ ያነሰ መስሎ ይገመት ይሆ ናል እንጅ ።

ትምህርት የማይለውጠውና የማያሻሽለው ሥ ልጣኔም የማያስከብረው ሕዝብና ሀገር ሊኖር አይች ልም ፤ ነገር ግን ይህንን ሁሉ ለማድረግ በቀደምት ነት የእነዚህን ፋና ይዘ የሚመራ ሁሉ እራሱን መስ ዋዕት አድርጐ ለሌላው ምሳሌ ካልሆነ በስተቀር በጥ ቂት አዋቂዎች ያውም ከተማ ውስጥ ብቻ ሆነን እን ተች በሚሉ ሀገር ልትለማ ሕዝብም ሊያድግ አይች ልም ። እስከመጨረሻውም ድረስ መስዋዕትነትን አሣ ምሮ በአጭርም ታጥቆ ስለ ሀገር ጥቅም የሚነገረ ውን ሁሉ በአሠራር ካላሳዩ ካልደከሙ መሻሻልን ማ የት አሻሽሎም ለሚአሻሽል ማስተላለፍ አይቻልም ።

የሚጠየቀው መስዋዕትነት ምንድነው ያልን እ ንደሆነ የከተማን ኑሮ ማጣት ብቻ እንጅ ከእዚህ በላይ ችግር አይኖርም ፤ ቢኖርም በእባብ ተነድፎ ወይም በወባ ተለክፎ መሞት ይሆናል ። ነገር ግን ላይቀር እንዳይደርስብኝ ብሎ በመሥጋት /ለመርዳ ትና ለመሥራት ሀገርንም ለማገልገል የሚቻልበትን ጊዜ በከተማ ፍቅር ብቻ ማሳለፍ የሚወድ ሁሉ የ ግል ጥቅሙን መስዋዕት አድርጐ ተምሮ ካላስተ ማረ ፤ ሠርቶ ካላሠራ ፤ አይቶ ካላሣየ በስተቀር የሚ ሠለጥን ተወራራሽ ትውልድ የምትበለጽግና የምታ ድግ ሀገር አለችኝ ብሎ ባይገምትና በመንቀፍ ብ ቻ ተነቃፊ ሆነው በሚጥሩት ትከሻ ላይ በመጨፈር ሊኖር አለመቻሉን እንዲረዳው ያስፈልጋል ።

የሀገር አስተዳደር የተወሳሰበ ፈትል ነው። በተለየም ብዙ ልማድና ብዙ ዓይነት ባሕል ብዙ ዓይነትም ስሪትና ብዙ ዓይነትም ጠባይ ባለው ሕዝብ ላይ ሲሆን፤ የበሰ ውስብስብ ያለ ነው። ይህ ንንም ለማፍታት ችግሩ የተወሳሰቢውም የአዋሳሳ ቢውም ሆኖ መፍትሄውም የጋራ መሆን ሊኖርበት አንዱ ሲቸገር ሌላው ለመርዳት አይሞክርም፤ አንዱ ሲነቅፍ የሚነቀፍበትን ነገር ሳይረዳው ተነቃፊውም ምክንያቱን ሳያውቀው እየሆነ መነቃቀፍ ብቻ የሥራና የመሻሻል መዝጊያ ሆኖ ቀርቷል።

ጉድለቶች እንዳሉ አይካድም፤ ጉድለትም ከማኅበራዊ ኑሮ አይለይም፤ ሰውም ይህንኑ አስተውሎ ለማኅበራዊ ኑሮ ዕድገቱ ሕግጋትን አደራጅቶ እራሱ በሠራው ሕግ ሥር ተዳዳሪ ሆኖ ለሠራውም ሕግ ተገዢነቱን አክብሮ የሚኖረው ስለራሱ ሰብአዊ መብቱ ነው። ጉድለትም ሲገኝ በለዘብታ፤ በማረም፤ ይራመዳል እንጅ በአንድ ጊዜ አሻሽላለሁ በማለት ግን አፍርሼ፤ ጥሼ፤ ልውጣ በሚልበት ጊዜ ዝብርቅርቅን ፈጥሮ በገዛ እጁ ሲያዘበራርቀው ጥፋቱ የማን ይሆን? የማይፈለጉትስ ጉድለቶች እየጐሉ ሊሄዱ አይደለምን?

በአሁኑ ጊዜ ኅብረት እንጅ የአሳብ መነጣጠል ለሀገሪቷ አይጠቅምም፤ ደግሞ በተለዩ ጥቃትና ጭቆና የማይወደው የሀገራችን ሕዝብ የሚተባበረው መከራ ሲደርስበት ብቻ ነው። ይህ ለምን ይሆናል? አንድ ክፉ ነገር በሀገሪቷ ላይ ከመድረሱ በፊት የሚደረገው መተባበር እንጅ ከደረሰ በኋላ በመቆጨት አይዘሀ ወንድሜ መባባሉ ዋጋ አይኖረውም።

ዛሬ የተያዘውና የሚታሰበው መነቃቀፍ ብቻ ሆኖ ይገኛል፤ መነቃቀፍም አርቆ ማስተዋል የሌለበት የአለ ይበሉኝና የወሬ ማዳነቂያ መደብር ሆኖ ከመገኘቱ በስተቀር ፍሬ አፍርቶ አልታየም።

ሰው በግል ቂሙ እንዴት የሌላውን ስም አጥፊ ይሆናል፤ ስለ ራሱስ ጥቅም ስለምን የማኅበራዊውን ጥቅም ይሰዋል?

የማይሠራ የሚሠራውን በያማና ለመሥራት ቢጣጣር እንዴት መልካም በሆነ ነበር።

በመመቀኛኘትና በመቀናናት መንገድ ከተሄደበት ነገር አይገኝም፤ እንደምንም ብሎ በጐ ሥራዎችን ከተረፉም በኋላ ሁለቱ ተንኰሎች ከመሐል ስለማይጠፉ የዕድገት እንቅፋቶች ሆነው ዘወትር ይገኛሉ። ከእነዚህም ሌላ ለእኔ ብቻ በማለት ንዋይን ከልክ አሳልፎ ማፍቀር ጉዳት ላይ ይጥላል፤ ጉዳቱም ለባለሀብቱ ብቻ ሳይሆን ማኅበራዊ ኑሮን ይዘ የሚጠፋ የማይጠገን ስሕተት እስከ መሆን ይደርሳል። በተለምዶና ዕድር ሆኖ በቆየን በሕል የሉም ምኞት በለሥልጣንን ደጅ ጠንቶ፤ ዥመት አግኝቶ፤ በተቀበለው አላፊነት ላይ ተዘፍዝፎ ለመኖርና እያሠራ ለመብላት ከሆነ ስሕተቱ ገና አልታረመም ማለት ይቻላል፤ ዕድገታችንም ሊሠራ አይችልም። ሲወርድ ሲዋረድ በመጣው በእዚህ ዓይነት ባሕል መኖር የሚመኙ ቢኖሩ ከሹማምንት እስከ ተራው ሠራተኛ ድረስ ይህንኑ ቢመኝ ምን ያስደንቃል? እንደሚመስለኝ የቀድሞው ገበር መግዘትና ሁሉም በኖአቅሙ ባለትዳር ሆኖ መኖር ምኞት ወይም እያንዳንዱ ገዢ ሆኖ መኖርን መምረጥ አለበ

ግን፣ የሁሉም ለእዚህ ጉዳይ መተባበር ከሌለ ምን ም ጊዜ ቢሆን ወደ እሚታሰበው መሻሻል ዓላማ መድረስ ቀርቶ መቃረብም አይቻል ይሆናል።

ተደጋግሞ የሚነገረው «መተባበር» ግዴታ ሊጠ ቀስ የሚገባው ቃል ሆኖ በመገኘቱ እየተደጋገመ ሊ ጠቀስ የአስፈለገው መተባበር ማለት ለሰው ልጅ ኑሮ ለዕድገቱ፣ ለምኞቱ፣ ለፍላጐቱ፣ ለሀገሩ ጥቅምና ይህ ንን የመሳሰሉትን ለሕዝብ ጠቃሚ ሆነው ይገኛሉ የ ሚባሉትን ጉዳዮች ሁሉ አጠቃሎ የያዘና ሊአሠራም የሚችል መሣሪያ እርሱ ብቻ መሆኑን የሚገልጽ ስ ለሆነ ነው። መተባበር ከሌለና ማንኛውንም የጋራ ጉዳይ አድርገው ካልያዙት እያንዳንዱ በየፊናው የ ሚሠራው ወይም የሚአደርገው የጊዜውን የግል ጥቅም ይሸፍን እንደሆነ ነው እንጅ፣ ለማኅበራዊ ኑሮ የተደላደለ ጥቅም እንደማይሰጥ እስከ አሁን የ ተደረገው ሊአስረዳ ይችል ይሆናል፣ እንዲያውም ያም ለግል ጥቅም ተብሎ የተሠራውም ቢሆን ምቀ ኛንና ቀናተኛን ከማበርከት ሌላ የሰጠው ፍሬ ይኖ ራል ተብሎ ሊገመት አይችልም።

የግል ጥቅምን ሙውደድ በለማወቅም ሊሆን ይችላል ወይም በንፉግነት፣ ባለማወቅ ከሆነ ምናል ባት ሊሻሻል ይችል ይሆናል በንፉግነት ከሆነ ግን የግል ጥቅምም ቢሆን ሰይዳብርና ለግልም ሳይሆን ለሌላው እንዲያው በክኖ የሚቀር ትርፍ ለመሆኑ አያጠራጥርም። የግል ጥቅሙን ብቻ የሚመለከተ ውን ደግሞ የአንድ ሀገር የእውነተኛ ተወላጅ ነው ብሎ መገመቱ ያስቸግራል።

ሰው በሀገሩ ይከበር፣ በሀገሩም ይኩራ እንጅ

ለዚያም በማንኛውም ዓይነት ማግበስበስ መበልጸ ግና ከፍ ብሎ መታየት በሁሉም ዘንድ ገና ተቀርጸ ስለሚገኝ ትንሹም ትልቁም ያገኘውን ዓይነት ሥራ መሥራቱን ነቅሮ በየመሥሪያ ቤቱ ደጃፍ እየተሰበ ሰበ የመንግሥት ሥራ ሲጠይቅ ሥራ የያዘውም የደመወዝ ዕድገትና የማዕርግ ከፍተኛነት ይሰጠኝ ሲል ይሰማል፣ ምናልባትም ከመቶ አቤቱታዎች መሃል ዘጠና ዘጠኙ ይኸው እንደሆነ አያጠራጥ ርም። እንግዲህ የመንግሥቱ መሥሪያ ቤት ብቻ የመተዳደሪያ ዓዳ ሆኖ ከተገኘና ከታዩ ሁሉስ ለም ን ጠያቂ ሊሆን አይገባውም? ይህንን የሚፈጥረው ዓይን አፋርነትና በተለይም ወገንን ብቻ ለመጥቀም በሚደረገው አንዳንድ ጊዜም ይሉኝታ በሌለበት አሠራር የአማላጆችም ከመንገድ በወጣ ማስቸገር ይህን ሁሉ ሊያደርስና ሊፈጥር ሊያስፋፋም ችሎ አል፣ ለምን ይኸ ይደረጋል ያልን እንደሆነ ያው የ ነበረብን ልማድ ገና ስለአልተለየን ሠርቶ መብላትን ሳይሆን አሠርቶ መብላትን ብቻ ስለምናስብ ነው። ይኸ ሊዘልቅ አማይችል ሊሆን የማይገባው ነገር ሁሉ ተቀጭቶ፣ ወድቆ፣ ሠርቶ፣ መብላትን ሠርቶ፣ መከበርንና መክበርን ማወቅ ግዴታ መሆን አለበት፣ የድብስብስም የቅሚያም የዘረፋም ሆነ የማጭበር በር ሃብት ከሕዝብ የሚለያይና ሀገርን የሚያጠፋ ተባይ መሆኑን አንዘንጋው።

የአንድ ሀገርን ሕዝብ የማይጠቅም ባሕል በአ ንድ ጊዜ ለማስጣል ባይቻል እንኳ በመጠኑ መንገ ድ ለማስያዝና ገሥግሶም ከፍተኛ ደረጃ እንዲደርስ ለመሥራት ይህንን ያህል አዳጋች አይሆንም፣ ነገር

በሀብቱና በማል ጥቅሙ ከተመካ ሀገሬ፣ ወገኔ፣ ባደ
ል ይሻለዋል። በሀብቱ የሠፋና የታወቀም ሰው ቢ
ሆን መከበሪያው ሀገሩ ነው፤ ስለዚህም በማሰብ ወ
ገኑንና ሀገሩን ባለመዘንጋት ሀብቱን አሥፋፍቶ ለሀገ
ሩ ዕድገት መሳተፊያ ከላደረገው፣ ወገኑን ረድቶ ከች
ግር እንዲወጣ ካልደገፈው፤ በሀብቴ ኩርቼ እኖራለሁ
የሚል ቢገኝ እንዴት እንደሆነ በሃሣቡ መጨነቅ
የእርሱ ፋንታ ነው። የግል ጥቅም አሳቢዎች ሲባል
የንዋይ ፍለጋ የሚአንቀዠቀዣቸውን ያልዘሩትን
ማጨድ የሚፈልጉትን በሆነውም ባልሆነውም ሌላ
ውን ወገናቸውን እየገፈፉ የዕለት ሆዳቸውን መሙ
ያና የማጭበርበር ሀብት ማጠራቀም የሚፈልጉትን
ልክስክሶች ብቻ ሳይሆን በሌላም መንገድ እራስን
ብቻ በመውደድ ሐሰትና ተንኰል እየዘሩ፤ ወንድ
ምና ወንድምን የሚአፋልሱ አፈ ጮሌዎችንም ይ
ጨምራል። እነኝህም የሚናገሩትን የማይምቱና
ወይም ሌላው የተናገረውን ቀልበው ሰያመዛዝኑ አ
ዋቂ ሆኖ ለመታየት ነገርን እየተቹ ልዩ ልዩ መልክ
የሚሰጡ ሁሉ መቅሰፍቶች ናቸው።

አንድ ሰው ደግሞ ልሥራ ማኅበራዊውን ኑሮ
ም ልጥቀም ብሎ በሚነሣበት ጊዜ የምቅኝነትና
የቅናት መንፈስ ያዘሉ አሽሙሮች ሲያሰሙት መል
ካም አሳቢነቱ ስግጥ ብሎ ወደኋላ ሲል ተስፋ ቆ
ርጦ የሚገኝም አይጠፋም፤ ይህስ ለምን ይደረጋ
ል? ለምንስ ያበጅ ይሆን?

ያሁን አንጅ በንጽሕና ሠርቶ ደክሞም ባገኘው
ሀብት ወገኑንም ጠቅሞ እራሱን ቢጠቅም ምንም የ
ሚያስነውር ነገር አይኖርም፤ ነገር ግን እራስን ብቻ

መውደድ በየአንዳንዱ ሳይ ሲታይ ብዙ እራስን ወ
ዳድ ማፍራት ይሆናልና፤ እራስን መውደድ በመጠኑ
ቢሆን ይሻሻል። «እኔ ከሞትኩ ሠርዶ አይብቀል»
ከሆነ ግን ተወራራሹ ሁሉ እንዲሁ ማለቱ አይቀርም
ና የኑሮን ደረጃ ማሻሻል፤ የሀገርን ዕድገት ማየትና
ማግኘት አይቻልም፤ በልቼ ልሙት ነውና ሁሉም
በልቶ መሞትን ከመመኘት በስተቀር ሌላ የተሻለ
አሳብና አሳቢነት ይኖረዋል ለማለት ያዳግታል።

ኧረ ለመሆኑ በሀገራችን አሉ የሚባሉት ከበር
ቴዎች ወይም ሀብታሞች እነማን ይሆኑ? በሀብታ
ቸውስ የሚቀናባቸው እነርሱም ሀብታሞች ነን ብለ
ው በሀብታቸው የሚኰሩ እነማን ናቸው? የሶስት
ጐጆዎች ባለቤት፤ የአንድ ጋሻ መሬት ባለእርሻዎች
ያውም ከእግር እስከ ራሳቸው በዕዳ የተነከሩ የባለ
ሽህ ብር ደመወዝተኞች ወይም በዳቤ በተገዙ ተ
ሽከርካሪዎች ተንፈላሳዮች አለበለዚያም በማጭበር
በር የሚያገኙት ኩንስንሶች ይሆኑን?

ይሽ ሁሉ እንኳንስ ሀብት መተዳደሪያ እንኳ
ሆኖ ሊጠራ አይገባውም፤ ይህንንም ስል እራስን
መውደድ ከማስጠላት አላማዬ ሳልዘባ፤ አሁን የ
ሚቀናበት ሀብት ያለው ኢትዮጵያዊ አለመኖሩን ወ
ደፊት ሲኖር ግን ምን ሊባል ይሆን? ብሎ ለማሳሰብና
የየአንዳንዱ ሰው ሀብት በበዛ ቁጥር የሀገሪቷ ሀብ
ትና የሕዝቧም ሀብት ሆኖ መገኘቱን ለማስገንዘብ
ያህል ነው፤ ሀብት ያለው ሰው ሀብቱን አሥፋፍ
ቶ ከሠራቢትና ሌላውም በመጠኑ በአቅሙ ሠርቶ
እንዲተዳደርበት ካደረገ ንፉግ ወይም እራስን ወዳ
ድ ሊያሰኘው አይችልም፤ ልዩ ልዩ ሰብዓዊ እርህ

ራሄ ያላቸው ከሀብታቸው ቆንጥረው ለልዩ ልዩ መረዳጃዎችና ለሰብዓዊም አገልግሎቶች ለበጐ ድር ጊቶች የሚሰጡም እንዳሉ ማወቅና የሌላውንም ሀ ገሮች ሀብታሞች ዝና መረዳትና መከተል ይገባል፤ ስለእዚህም በእውነት ሠርቶና አሠርቶ በወዙም ደ ክሞ ለሁሉም ለአገሪቷም ለመጥቀም በሚችል ሰ ው ላይ ነቀፌታንና ቅናትን ማውረድ ተገቢ አ ይሆንም ።

ሀገራቸውን ንቀውና ነቅፈው በእውቀታቸው ተመክተው ደሀ ወገኖቻቸውን መርዳትና በተለየም በአሁኑ ወቅት ሀገራቸውንም ማገልገል ሲገባቸው ለራሳቸው ምቾትና ለግል ጥቅማቸው ብቻ በመጓጓ ት አንድአንድ ሀገራቸውን ትተው የሚገኙ ሁሉ እ ንደዚሁ ራሳቸውን ወዳድ ከመባል ሌላ ሰነፎችም ተስፋ ቢሶችም ናቸው ። በእነርሱም ላይ፤ « በሰው ሀገር ያጌጠና ዱር ገበቶ የዘፈነ አንድ ነው » የተባ ለው ምሣሌ ይፈጸምባቸዋል ።

ምዕራፍ ፫

ሀገራችን ደሀ አይደለችም የሕዝቧም እሩሀሩህ ነት ችግረኛ ወገኖቹ በረሀብ እንዲሞቱ አያደርግም፤ በዚያችው ባለው መሣሪያ አርሶም ይሁን ቆፍሮ የ በተነ ይነስም ይብዛም የተረጋገጠ መኸር ያገኛ ል፤ ነገር ግን መሬት ላይ ተቀምጠ መሥራትን የ ማይወድ ሁሉ ችግረኛ ሆኖ ይገኛል ። የሀገራችን ዋናው ሞያ እርሻ እንደመሆኑ መጠን ይህ አየተዳ ከመ የሚሄድ ከሆነና ሁሉም ዋሞያተኛ ልዩ ልዩ

ሥራዎች ፈላጊ ሲሆን፤ በልዩ ልዩ ሥራዎች በመ ጠመድ ሠራተኛው ብዙ ገንዘብ ለማትረፍም ቢች ል በገንዘብ ገዝቶ ሰውነትን ሊቀልቡ የሚችሉት ሁሉ ካልተገኙና ካልቀረቡለት በስተቀር ገንዘብ ስንቅ ሆኖ ስለማይገኝ ይህም ሁናቴ ችግረኛን እን ደሚያበዛ አያጠራጥርም፤ ስለእዚህም አራሽ ገበሬ ዎች የሚበረታቱበትንና አሠራራቸውንም የሚአሻ ሽሉበትን ምርታቸውም ገበያ የሚአገኝበትንና የ ውስጥ መገናኛ መንገዶችን ማደራጀት ግዴታ ይ ሆናል፤ ይህም በማስረዳትና በማሳየት ሊፈጸም ይቻላል ።

በቀድሞ ጊዜ ስለ አንበጣ መፈልፈልና ሰብል ን ስለማጥፋት ሲነገር፤ አንበጣ እህል አጠፋ ተብ ሎ ከተነገረ በኋላ ስለ ረሀብና ችግር እምብዛም ተሰምቶ አያውቅም ። በአሁኑ ጊዜ ግን ከአንበጣ መፈልፈልና ሰብል ከማጥፋት በኋላ ረሀብና ችግር ማስከተሉንና የአራሹም ወገን ሥጋት ይሰማል፤ ይሁን እንጅ ቀድሞ ይመጣ የነበረውና አሁንም የ ሚመጣው አንበጣ አበላሉ እኩል ሊሆን ይችላል፤ ነገር ግን አስተራረሱ እኩል ስለ አልሆነ ደግሞ በአንድ በኩል አራሹም ስለ ተቀነሰና በላተኛው ሕ ዝብ ከቀድሞው ጊዜ የበዛና የበለጠ በመሆኑ ከአን በጣው መንጋ አጠፋፍ የተረፈው ሰብል ለበላተኛው የማይበቃ ሆኖ መገኜቱ የተረጋገጠ ይመስለኛል ።

ከሞላ ጐደል የሕዝቡ ጤና ተጠብቋል፤ ዛሬ መድኃኒት ገዝቶ የማይውጥ የለም፤ የዘርን ማብ ዛት ጠንቅ ሆኖ ይገኝ የነበረው የ..... በሽታ በጣ ም እየተቀነሰ ሄዷል፤ የቀድሞዎቹ የልጆች አስተ

ዳደግና የዛሬው ምንም በሙለ በይዳረስ ትልቅ ልዩነት አሳይቷል፤ ይህም እየቀጠለ መሄዱ ስለማ ያጠራጥር የወደፊት የልጆች ዕድል የበለጠ እየተ ቃናና ከዓመት ወደ ዓመት እየተሻለ መሄዱ አያጠ ራጥርም፤ በእዚህም ዓይነት ሲቀጥል ሕዝቡ እየበዛ ይሄዳል፤ ሕዝብም በበዛ ቊጥር ችግሩ እየበዛ መሄ ዱ እርግጥ ነው፤ የሚታሰብበትም ጊዜ ከአሁኑ ጀ ምሮ ስለሆነ ይህንን ሁሉ ለማድረግ ለመሥራትና ለመደርጀት የሚቻለው በሕብረት ሲታሰብበትና ሁ ሉም ለመሥራት ታጥቆ ሲነሣ እንጅ በምኞትና ለ ምን አይሆንም በማለት የእራስንም ምኞት መርጠ አንድ በታ ላይ ተቀምጠ በመተዥት ብቻ አይደለም።

እንሥራ ካልን መሥራት እንችላለን፤ ሁላችንም የፊት የፊታችንን ለነገ ሳንል ከገፋነው የበታችም ኃላፊነቱን አውቆ እንዲመራ ከሆነና በበላዩ በማመ ሀኘት ለከፍተኛ ባለሥልጣን አድርሼአለሁ እያለ ከመለገም ከወጣ ከፍተኛ ባለሥልጣንም ምን ላድ ርግ በማለት ካላፊዘ የጋራ ኃላፊነትን ይዘን በመተ ማመን ከሄድን የማይሠራ ነገር ሊኖር አይችልም።

የአንድ ሰውን የሥራ ትጋት የሚቀጩና ተስ ፋ የሚአስቀርጡ ነገሮች ሊደርሱ ይችሉ ይሆናል፤ ይሁን እንጅ ሃሳብ ጽኑ ከሆነና ሀገሩንም ከፈቀረ ማንም ወደኋላ ማለት አይገባውም አለበለዚያ በእ ዚህ ዓይነት ተስፋ መቊረጥ የሚከማቹው ዘርፍ የልግም ቀለብተኛ ሆኖ ከመቀመጥ በስተቀር ሀገ ሩን ሊረዳ አይችልም ከመወቀስም አይድንም።

የተፈጥሮ ሕግ ሆኖ ሰው ሁሉ የእኩልነቱን መብተ ሳይለቅ አንዱን አስተዳዳሪ አድርጐ በሽም

ግልናውም ቢሆን መርጠ አለበለዚያም አንተ ትብ ስ ትሻል ወይም ታውቅ ብሎ በመከባበር አስተዳ ድረን ምራን ዳኝን ብሎ ይመርጠዋል፤ ይህም የትህ ትና ፍሬ ስለሆነ ነው። ከእዚሁ ከተፈጥሮ መብት ጋር የተያያዘው የያንዳንዱ መብት ሲወርድ ሲዋ ረድ መጥቶ ማሕበራዊ ኑሮን ለመመሥረት ሕግ ጋት ስለአስፈለጉ ከጊዜ ወደ ጊዜ የተሻሻሉ ሕግ ጋትና የጠቅላላውን ሰብአዊ መብቶች የሚጠብቁ እድሮች እየተሠሩ ሄደው ይኸው በሕግጋት ሥ ር ተዳድረን እንገኛለን፣ እንግዲህ የሰው መብት በተፈጥሮም በሕግም እኩልነት እንዳለው የተረጋ ገጠ ነው።

የተፈጥሮ መብቶችን ምንም ነገር ሊለውጣ ቸው አይችልም፤ ሕጋዊ መብቶችን ግን ብዙ ጊዜ ቀጣት የማያስከትል ትሕትና ሲጥሳቸው ይታያል፤ ትሕትናም ለሰው ልጅ ጠቃሚና በተለየም የጨዋ ነት ምግባር ስለሆነ አንዱ ለአንዱ በትሕትና መን ገድ የሚአሳየው መልክ ወይም ሁናቴ ግዴታን ያስ ተከለ መስሎ መገመት አይኖርበትም ትሕትና የተ ደረገለት ስለተከበረ ወይም ከፍ ስለአለ አድርገ ቢቆጥረው ተሳስቶአል፤ ትሕትና አድራጊውም ስለ ትሕትና ብሎ ያድርገው እንጅ እራስን ዝቅ አድ ርጐ በማየት የበታችነት ተሰምቶት አይሁን። ለሰ ው ልጅ መከባበር መወዳጀት አንተ ትብስ አንተ ትብስ መባባል አፋቃሪ መሣሪያ መሆኑ አያከድም ይህም ከተፈጥሮ ሕግ የወረደ ለመሆኑና በመጽሐ ፍትም የታዘዘ ስለሆነ ከጉዳቱ ጥቅሙ ስለሚያመ ዝን ሁላችንም እንጠቀምበታለን።

በተለየም በሀገራችን ትሕትና የላቁና የነገሠ ሆኖ ሣለ እየቀዘቀዘ ሲሄድ መታየቱ አሳዛኝ ነው። ትሕትና ጥሩ ነው፤ ትሕትና አከባባሪና አፈቃቃሪም ነው፤ ይሁን እንጅ ትሕትና ከልክ ያለፈም ሲሆን አያስደስትም፤ ከልክ ያለፈ ትሕትና ማለትም ለም ሣሌ ያህል ጫማ መሣም ወይም እስክ መሬት ዝቅ ብሎ ግምባር ምድር እስቲነካ ድረስ እጅ መንሣት ዝቅተኛነትን ማሳየት ይበላል እንጅ ትሕትና አይደለም ወይም መሸርደጃ መለማመጫ ሆኖ ይገመታል። ይህንን አደራረግ ትሕትና ነው ወይም የጨዋ ባሕላችን ነው ብሎ የሚገምት ቢገኝ ዘመኑ ያለ ፈበት ባሕልና ትሕትና መሆኑን ማወቅ አለበት።

ትሕትና ሲጠፋም ሲጐድልም መልካም አይደለም፤ ቅደም አንተ ተቀመጥ መባባል፤ ወይም ለሽማግሌ መነሳት፤ ሽማግሌን ማክበር፤ ታላቀን ማክበር የትልቀና የትንሽነት የበላይና የበታች የባለሥልጣንነት መባባልም ሣይሆን እኩል ትሕትና መለዋወጥ ጨዋነት ነው ስለእዚህም አግቦ ሽርድ መለማመጫ ጠቅላላውን ዋጋ ቢስ ትሕትና ከማድረግ አለማድረጉ የተመረጠ ነው የእውነተኛ ትሕትና ፍቅርን ስለሚአተርፍ በእውነተኛ ትሕትና መገናኘት ይገባናል።

ደግሞ አንድ የግብር ይውጣ ወይም የለበጣ ሣይሆን በአዛኝና በታዛኝ መሀል ወይም በሹምና በበታች መሀል ዘወትር ጉልህ ሆኖ የሚታይ መሸቀርቀር አለበለዚያም የአይን ማፈር ነገር አለ። ለም ሣሌ ያህል ከአንድ ባለሥልጣን ጋር ወይም ከአንድ የተከበረ ሰው ጋር አንድ ሌላ ሰው ሲገናኝ ወ

ይም ሲነጋገር የመሽኰርመም የመቅለስለስ የማፈር ነገር ያሳያል ወይም ይታያበታል፡ ቁጭ በልም ሲሉት ወንበሩን ሳብ እራቅ አድርጐ ያለመዝናናት ይቀመጣል፤ ይህ አደራረግ ትሕትና አይደለምና ዝቅተኛነትን ማሳየት እንዳይሆን ትሕትናን ለብሶ ከማንም ጋር ሲገናኙ ሲነጋገሩም ቢሆን ሰብአዊ መብትን እኩል አድርጐ ቆጥሮ መገንት ይገባል። በእዚህ አገላለጤ ላይ ትሕትና ይቅር ትሕትና ይጉደል ማለቴ ሣይሆን ትሕትና ይጉላ ይኑር፡ ነገር ግን ከመንገድ የወጣ ትሕትና ሣይሆን ሁለም በሚገባው መንገድ ይደረግ ብዬ ለማሳሰብ ያህል ነው።

በሀገራችን ትሕትና እየቀዘቀዘ ሄደ ስል ደግሞ ብዙ ትሕትና የገደላቸው አሰራሮችና አነጋገሮች እየገሉ መሄዳቸውንና ሊታረሙ የሚገባቸው መሆኑን ለማስገንዘብ ነው።

የሀገራችን ሰው በተፈጥሮው ሰው አክባሪ እንግዳ አስተናጋጅ በተለየም ችግረኛ ረድኤና ለወገኑ አሳቢ እንደሆነ አያጠራጥርም፤ ይሁን እንጅ ዛሬ ወደ መቅረቱ እያለ ሲያዘግም የሚታየው ጨርሶ ሊጠፋ ላይተካ ይችላልና በጊዜው ተረዳድተን ትሕትናንና፤ ለሰው ቅን መስራትን የመሳሰሉትን ሁሉ ሳያመልጡን ጨብጠን መያዝ ያስፈልገናል።

አንዳንድ ጊዜ የሚደርሰው የሚታየው የሚሰማው የሚአማርር ነገር የሰውን አንጀት የሚአሻክር ነው። በጠቀላላው አነጋገር ትሕትና ለትልቅ ለትንሽ ለባለሥልጣን ለሹማምንት ለበላይ ለበታች ሳይበል ለትሕትና ብሎ ስሙም ተሠርዞ እንዳይቀር ትሕትና እንዲኖርና ትሕትናም እንዲሠራበት አስፈላጊ ነው።

«መታዘዝን ያላወቀ ማዘዝ አይችልም» እንደ ሚባለው የማዘዝና የመታዘዝ ነገሮች በማሕበራዊ ኑሮ ያሉና የማሕበራዊም ኑሮ የፈጠራቸው የሰው ልጅ መተዳደሪያ ሕግጋቶች እንጅ ሰው አዛኝና ታዛዥ ሆኖ ተፈጥሮ አይደለም፤ ይህንንም ከወቅንና ከተረዳነው ዘንዳ ስለራሳችን ስለ ማሕበራዊም ኑሮ አችን አራሳችን ባበጀናቸው በአቋቋምናቸው ሕግ ጋት ሥር ተገዥ ሆነን እንድንተዳደር አድርገናልና አዛኝና ታዛዥነታችን ለእኛው ደምበኛ መተዳደሪያ መሆኑን አጥብቀን መረዳት አለብን። አንዳንድ ሰዎች ሲተቹ እገሌ የተፈጠረው ለማዘዝነው ወይም እኔ የተፈጠርኩት ለማሽቆጥቆጥ ነው ይላሉ ይህም የተሳሳተ ግምት መሆን አለበት አዛኝነትም ታዛዥነትም በሕግና ስለ ሕግም ነው ከእዚህም አልፎ ተርፎ ብልህነትንና ዕድልን ይጠይቃል ስለእዚህም ማዘዝና መታዘዝ ሁለቱ ምን እንደሆኑና ለምንስ እንደሚጠቅሙ አጥርቶ ማወቅ የበለጠ ብልህነትና ስለ አንድነትም ፍቱን መሣሪያ መሆናቸውን አጥብቆ መገንዘብ ነው። ማዘዝም መታዘዝም በትሕትና ከሆነ ደግሞ ውጤቱ ያማረ መተባበር እንደሚያፈራ አያጠራጥርም።

የሰው እውቀቱና ብልህነቱም ከሀገሩ ባሕልና ልምድ ጋር ተያይዘ የሚሠራ መሆን አለበት በእዚህም እይነት አሠራር የአንድ ሀገር እድገትና ለውጥ አየተሻሻለ እንደሚሄድ ጥርጥር የለውም ግን በአየሁትና በሰማሁት አይነት በአንድ ጊዜም አደርገዋለሁ ብሎ መነሣት ቀርቶ ማሰብ እንኳ ትልቅ ስሕተት ይሆናል፤ ይህንንም ማድረግ የሚቻላቸው

ቢኖሩ የእኔ አስተያየት እንቅፋት ሊሆናቸው እንደ ማይችል እመኻለሁ ደግም እሚሆን ከሆነ ከእዚህ የተሻለ ምንም ሁሉን አስደሳች ነገር ሊኖር አይችልም። ብዙ ምሣሌዎች ሰምተናል ብዙ ታሪክችም ተከትለናልና መዘርዘር አያሻም እንግዲያውስ ይህ ከሆነ እራሳችንን ከእኩዮቻችን ጋር እያወዳደርን አመራራችንና ፍላጐታችንን እየቀረዳን እንደግ እንጅ ከብዙ ጊዜ በፊት አድገው ደርጅተው ተስፋፍተውና ተራቅቀው ጨረቃን እንዳስ ከሚሉት ጋር ምኞታችንን እያወዳደርን በስንፍናና በተስፋ መቁረጥ የእኛ ነገር እያልን በራሳችን ትዳርና ኑሮ ስናፌዝ ከተገኘን ውለን አድረንም እዚያው ላይ እንደምንገኝ አይከድም።

ሁላችንም ወቃሽና ነቃፊ ከሆንን ዘንዳ ደግሞ ተወቃሹና ተነቃፊው ማን ሊሆን ይሆን።? ይህንንም ስል ጽሑፌ ማሳሰቢያ እንጅ ወቃሽ ሆኖ እንዳይገመት እየለመንኩ ነው።

እንግዲህም መግባባት መተባበር መተዋወቅም ከደረብን ድካማችን የጋራ እንዲሆን ትግል ይኖርብናል ይህንንም አውቀን የምናደርገው ከሆነ እምብዛም ችግር አያጋጥመንም። ተባብረንም በአንድ መንፈስ፤ በአንድ መልክ፤ በአንድ አካልነትም፤ እንሥራ ሀገራችንንም በእውነት በቅንነት እናገልግል ስንል የእሠሪውም የሠሪውም መሣሪያ የሆነው ነገር ከወዴት የሚል ስሜት በየአንዳንዳችን መታሰቡ መነገሩ አይቀርም፤ ይሁን እንጅ አስቀድሞ ሊታሰብበት የሚያስፈልገው ለመሥራት ታጥቆ የመነሣቱ

ዓላማ መሆን አለበት ባይ ነኝ። ስለ ሌላውም ቀጥ ሎ ይታሰባል።

ዛሬ ሁሉም ሠራተኛ ሁሉም ደከመኝ ባይነው እርግጥ ሠራተኛም አለ ብዙ የተሠሩም ነገሮች ይኖራሉ ግን መልክ የያዙ አይደሉም። ደከመኝ ባይም የድክምና የመሥራት ፍላጐት መቀነስ ሳይ ሆን የቅጥ ማጣትና የአሠራሩ መንገድ አለመያዝ ብቻ አስንፎት የአንጐል መወሳሰብ ያንንም ያንንም ስለሚያስዳስሰውና የመዳሰሱም ፍሬ ዝብርቅርቅ ሆ ኖ ስለሚታየው ወደ መሰልቸት ያዘነብላል። ይህን ንም ሊአስቀር የሚችለው ሥራን በወጉና በቅጡ በጊዜውም እንደአስፈላጊነቱ በማደራጀት ሲመሩት ነው እንጅ በምንቸገረኝነት ከያዙትና አልፎ አልፎ የሚከሰተውን አለበለዚያም ብልጭ የሚለውን ብቻ እየጠበቁ ሠራው ቢሉት ሊሠራ የሚገባው ታልፎ ጠቃሚነቱ ገና የሚሆነው አለጊዜው ጐልቶ ይገ ኛል፤ አስፈላጊ የሆነውን ደግሞ ለመሥራት ሲታ ሰብ እንደገና ወደኋላ መመለስ ይሆናል ይህም አሠ ራር፤ እየካቡ ማፍረስ እንደሚሆን ጥርጥር የለውም፤ ስለአዚህ ለአሠራር ቅጥና ወግ ማስፈለጉ እርግጠኛ ለመሆን ብቻ ሣይሆን ተገቢም ነውና የአሠራርን ዘዴና ትልም ወግና ቅጥ ሁላችንም በየግል ሥራች ንም ቢሆን ማወቅና መልመድ አለብን፤ እንደዚህ ያለውንም ሥርዓት ከለመድን ዘንዳ ሐብታችንንም ሆነ ጉልበታችንን እንቆጥበለን መንፈሳችንም ረክ ቶ አንጐላችንም ሊአስብ ይችላል፤ ደከመኝ ማለ ትም መሰልቸትም ይቀነሣሉ የጀመርነውንም መጨ ረስ መቻል እናውቃለን።

የሕብረት ሥራ ቁምነገር ነው፤ ቁምነገርም ለማ ፍራት ያስችላል ስለእዚህም ተባብሮ መሥራትን አዋጥቶ ለሥራ ገንዘብ መመደብን ከለመድንና መረ ዳዳትን ከመንበት እርስ በርሳችንም ከተማመንን ል ንሠራ የማንችለው ነገር አይኖርም።

መሻሻል በጣም አስፈላጊ ነው፤ ስለእዚህም በመ ሻሻል መንገድ ላይ ገብቶ የሚጓዘው ሕዝብ የመሻ ሻሉ ዘዴ በሚገባ እንዲሆን ሊአሳዩት፤ ሊመሩት የተገባቸው ወገኖች የራሳቸውን መሻሻል ብቻ ተገ ን አድርገው ስለሌላው አለመሻሻል ቢናገሩት ቢተ ቹት ዋጋ ሊኖረው አይችልም፤ መሻሻልም ማለት በአለባበስና በመሸኰንተር አነጋገር በማሳመርና ስለ ሌላው ሀገር ሥልጣኔና ዕድገት በመናገር አይደለም፤ ነገር ግን ለእዚያ ለእውነተኛው ባላገር የእውነተኛ የእርሱ መሻሻል ምን ቢያደርግ እንደሆነ ግልጥ ባለ በሚገባው አነጋገር ቢአስረዱት ሊጠቀምበት እንደሚችል አያጠራጥርም ቀን መንፈስ ያለን ብን ኖርና በወር አንድ አንድ ቀን እንኳ የዕረፍታችንን ጊዜ ሰውተን በቅርብ በሚገኘው አገር ቤት አን ዱን ትንሽ መንደር መርጠን የቤትን ጽዳትና አያ ያዝ የንጽሕናን ኑሮ የሌላውንም የመሻሻልን ጣዕ ም ደጋግመን ብናሳይና ብናስተምር ስለ ወገንም ፍቅር ብለን ብንደክም በእዚህ ዓይነትም ይህንን የመሳሰለ ነገር እየተስፋፋ ቢሄድ ለእዚህም አይነት ሥራ ብዙ ደጋፊዎች ቢገኙ በትንሹ የተጀመረው ተቀጣጥሎ የማይዳረስ ይሆንን? ምጣኔነቱስ እየተ ስፋፋ የማይራብ ነውን? አንዱስ ከአንዱ እያየ መሻ ሻል ለብዙው ሳይዳረስ ይቀራልን? አንዱን ሰው

ከሰዩት በመንፈስም ከአጽናኑት ከአመለከቱትና ከኑ
ሮ ጋር እንዲተዋወቅ ካደረጉት የሚለይዱትን ሁ
ሉ ሊቀበል እንደሚችል አይጠረጠርም ፤ ይህንንም
ለማድረግ ብዙ ነገር ብዙም ወጭ አይጠይቅም እን
ድ ባላገር ለጊዜው እንኳ የተደላደለ ትዳር ቢያኖ
ረው በዚያው ባለችው ጸድቶና አጽድቶ እንዲገኝ
ለማድረግ ምክርና ማስረዳት ብቻ ነው የሚጠይ
ቀው ሌላውን የሚሠራው ግን እርሱ ነው ፤ ይኸም
ቀላልና በጣም ትንሽ ምሣሌ ለመግለጥ ያህል ተጠ
ቀሰ እንጅ እንደዚህ ያሉ በቀላሉ ሊሠነዘሩ የሚ
ችሉ ብዙ ነገሮች መኖራቸውና በቀላሉም ሊፈ
ጸሙ የሚገባቸው ስለአሉ አሁንም ያዬ ሁሉ ለማሳ
የት ታጥቆ መነሣት አለበት ፤ እይሆንም የሚባል
ከሆነ ግን እነ ሽክስፒየርን እነ ቪክቶር ሒጐን የመ
ሰሰሉትንና የሄድሮፒንን ፤ ጨረቃ ላይ የመውጣ
ትን ውይይቶች ከግብ፣ ቤት ጓዳ ውጭ የማያልፉ
ትን ጉዳዮች ብቻ በመነታረክ ጊዜውን ማሳለፉ
ያጠቅማል ከተባለ ሥልጣኔውም እስከዚሁ ድረስ
ከበቃና በተሰፋ መቅረጥ ከተሄደ ነገሩ ሁሉ እዚሁ
ላይ ያልቃልና ነገ እንምራህ የሚባለው ሕዝብ ሊአ
ገድ ይችላል የአሁኖቹም ወጣቶች ሌላ ወጣት ሲመጣ
ባቸው ተነቃፊነታቸውና ተጠይነታቸው እንደ አሁኑ
ተነቃፊዎችና ተጠይዎች እንደሚሆኑ አይከድም ።

ጊዜና ትውልድ የአቀራረባቸው በአንድ ገበ
ታም ትምህርት የተሳተፉ ጓደኞች ይተዋወቃሉ ፤
ስለእዚህም መተዋወቅና ጓደኝነት አስተሳስሮአቸው
ስለሚገኝ በሚሠማሩበት በየክፍል ስራቸው በሚኖ
ሩበት ጊዜ መወያየትና መጠያየቅ አሳብ ለአሳብ

መለዋወጥና መተዋወቁ ሊአገናኛቸው ይኖራል ።
በመተማመንም በሕብረትም ሊሠሩ ይችሉ ይሆ
ናል ፤ ነገር ግን ከእነርሱ በኋላ ከሚወጡት ጓደኞ
ችና ወገኖች ጋር የሚአቀራርባቸውና የሚአስተዋ
ውቃቸው በአንድ አሳብም እንዲመሩና እንዲሰለፉ
የሚአደርጋቸው አገናኝ ጥርጊያ ከሌለ ከፍ ብሎ
እንደተጠቀሰው ያለ ጉድለት ማስከተሉ ስለማይቀር
የሚታሰብበት እንዲሆን ያስፈልጋል አለበለዚያ የጥ
ላቻ መወራረስ ሆኖ መሻሻል የለም ።

መሻሻል ማለት በጥቂቶች ላይ ተወስኖ የሚ
ቀር ማለት አይደለም ፤ ከእስከ ሣይሆን ለሁሉም መ
ዳረስ ይኖርበታል ፤ ለሁሉም በተዳረሰ ጊዜ ደግሞ
የየአንዳንዱ የኑሮ ደረጃ ከፍ ባለ ቅጥር መሻሻሉ
ያለ ድክም አውቆ ይመጣል ፤ የየአንዳንዱ የኑሮ ደረ
ጃ እንዴት ከፍ ሊል ይችላል የሚል አሳብ ላይ
እንወድቅ ይሆናል ፤ እርግጥም አስቸጋሪ ጥያቄ ነው
ይሁን እንጅ የሕዝቡን የኑሮ ደረጃ ለማሳደግ ማድ
ረግ የሚአስፈልገው ሙከራ ለጊዜው የማይጠቅሙ
ትን የቅንጡ ሥራዎችን አግዶ ለአስፈላጊዎቹ ሥራ
ዎች ቅድሚያ ሰጥቶ መሥራቱ ጠቅላላ መልስ ይሆ
ናል ብዬ አምናለሁ ።

መሻሻል ማለት ከበሕልና ከልማድ እርቆ መለ
የት ማለት አይደለም ፤ ወይም በሰው ሀገር በሕልና
ልማድ ሰልጥኖ ሌላውም በዚያው ዓይነት ልማድና
በሕል ካልተመራ አልተሻሻለም ብሎ መገመትና ዝ
ቅም አድርጐ ማየት አይደለም ፤ መሻሻልም የጋራ
ካልሆነ ለሁሉም በመጠኑ ካልተዳረሰ የጥቂቶቹ መ
ሻሻል ብቻ በብዙው ባልተሻሻለው ጥላ ሥር ሲገኝ

በባዕድ ተመልካች ዘንድ ማንም የተሻሻለ እንደሌለ እርግጥ ነው ስለእዚህም ተሻሻልን የሚለው ወገን፣ ገና ያልተሻሻለው መሻሻል ነው ብሎም የማያምን በትን ከበሕሉ ውጭ የወጣ ነገር አድርጐ ማሰየት በተደረገውም ባሕል ወጥ ጉዳይ ነቃፊ ሲገኝ የት ይገባዋል ገና ደንቆሮ ነው ወደኋላ የቀረ ነው ብሎ ከማለት ይልቅ ነቀፌታውን አዳምጠ አስረድቶ ማሳ መን ወይም ተረድቶም እንደሆነ መታረም ይገባ ይመስለኛል ።

ከበሕላችን ውጭ የሆኑ ይጠቅሙናልም ብለን የማንገምታቸው ያልታረሙ የውጭ ባሕሎች ወደ ሀገራችን ዘምተው መግባታቸው አይከድምና ጠቃ ሚዎች የሚሆኑትን ብቻ መርጠን መያዝ አለብን ።

« የተናገሩት ከሚጠፉ የወለዱት ይጥፉ » ሲባ ል ስንሰማው የነበረ የቃልን ማክበር ምሳሌ በአ ሁኑ ጊዜ ሰልስሎ በመንገዳገዱ እጅግም ሲጠቀስ አይሰማም ይህም የሚአስገነዝበው ቃል ማክበርና በቃልም መገኘት እየወደቁ መሄዳቸውን ነው ፤ እን ደ ምሳሌው ከባድነትና አስገንዝቢነት ልንረዳው የሚገባን ከወለዱት ይልቅ የተናገሩትን ማክበር ነው፤ በቃልም መገኘት ከሁሉ የበለጠ ቁምነገር ነው ማ ለት ነውና የቃል ማክበር ነገር ቅድሚያ ተሰጥቶት አብሮ እንዲሰለጥን መድከም የሕዝብን ጽኑ መን ፈስ ዕድገት ማነጽ መሆኑን ማመን ነው ።

እንግዲህ በነካ ነካ ይጠቅማሉ ብዬ የገመትኳ ቸውን ማሳሰቢያዎችና በጣም ትንሽ የሆኑትን ምክ ሮች በእዚህ ውስጥ አሳርፌአለሁ ። የመሰለኝን ለጊ ዜውም ይጠቅም ይሆናል ብዬ የገመትኩትን በአ

ጭራና በቶሎ ለማቅረብ በመገደዴ አነጋገሬ መልክ አልያዘ ይሆናል ፤ ይሁን እንጅ ምን እንደሚል ይገ ልጻል ብዬ አምናለሁ ።

ዋይ ዋይ ከማለት በፊት መወያየት ቢቀድም ብዙ ክፉ ነገሮች አይደርሱም ፤ እርስ በእርስም መግ ባባት ከኖረ በሕብረት ለመሥራት አያዳግትም ።

ምቀኝነት ፤ ቅናት ፤ ተንኰል ፤ ሐሰት ፤ ጉበ ፤ እምነ ት ማጉደልና አድሎ እነዚህ ከቀሩ ማንኛውም ነገር ሁሉ ቀጥ ብሎ በንጹሕ መንገድ ሊሄድ ይችላል ፤ እነዚህን ደግሞ ለማስቀረት የሚችለው ንጹሕ ሕሊ ና ብቻ ስለሆነ ሕሊናችንን ለማንጻት እንታገል ።

ምዕራፍ ፬

እስከ አሁን እየተራመድንም እየዘለልንም አል ፈን ይሆናል ፤ አሁን ግን መሸጋገሪያ ድልድያችንን አጥብቀን መገንባት አለብን ፤ ይህንንም ለማድረግ የየ አንዳንዳችንን እርዳታና ቆራጥነት ይጠይቃል ፤ እርዳ ታና ቆራጥነትም መብትን ማወቅ ስለሚጠይቁ ምን ም ሁላችንም መብታችንን ብንረዳውና ብናውቀ ውም ሥራ ላይ ውሎ እንዲገኝ ለማድረግ ሞክረ ንም አልሞከርንም ይሆናል ፤ የሆነ ሆኖ የያንዳንዱ መብት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ መልሶ መላልሶ መሞከር አለብን ፤ ይገባልም ፤ መብት ከተጨ በጠ ከተከበረና ከኖረ የመሸጋገሪያው ድልድይ ተ መሠረተ ማለት ነው ፤ የሚጐድለው እየተሞላ ሲሄ ድ ደግሞ አሁንም ድልድዩ ተገነባ ቅርጹና መልኩ ተሰጥቶት የመሸጋገሪያው ወገን ከተዘረጋ በኋላ መሸ

ጋገር ቻልን ማለት ነው፤ ይህም ከሆነ ሁሉም በሥነ ሥርዓት ይተላለፋል ይሸጋገራል እንጅ ከሥነ ሥር ዓት ውጭ ልሂድ የሚለው ሊታገድ ይችላል። የመብትም ልኩ የት ድረስ እንደሆነ ሲታወቅ ሁሉም መብቱ መስሎት ይገምት የነበረው ሁሉ የመብቱን ወሰን ሲረዳው አውቆ ይገታል። እምብዛም የጐደሉ መብቶች በይኖሩ ወግና ቅጥ ስለሌልያዙ ያሉት የተሠሩት ሊደረጉ የሚገባቸው ሁሉ ተበታትነው በመገኝታቸውና ሰብስበ እንዲሠምሩ የሚአደርጋቸው አካል በመላላቱ እንደሌሉ ተቆጥረው ሁሉም በየበኩሉ በመሰለው በየአይነቱ ሲተችባቸውና ሲነቅፋቸው ይሰማል። ሰውነትን የሚያንቀሳቅሰው አንጐል መሆኑ የታመነውን ያህል መንግሥትንም የሚያንቀሳቅሰው የሚመራው ትክክለኛ አቋም እንደሆነ አይክድም ይህም ትክክለኛ አቋም የመሪዎች አንድ አካል ሆኖ መገኘት አለበት።

የመሪዎች አለመተባበርና አለመግባባት፤ ለአንድ ጉዳይ መሰለፋቸውን አለማወቅ እየሆነ መተማመናቸው እያጠራጠራቸውና እርስ በእርሳቸው እየተመከኛኙ የግብር ይውጣ በሆነ ነገር ሲነታረኩ ሲታይ «ድንጋይ ምን ያስመሀላል ውሀ፤ ውሀ ምን ያስመሀላል ድንጋይ» እንደሚባለው ዓይነት እየሆነ፤ የሥራው ፍሬ እያዘቀጠ፤ ለጉዳዩ አላፊና ተወቃሽ ወይም ተጠሪና ተጠያቂ አይገኝም፤ እዚህም ላይ ጐድሎ የሚታየው ያውያለመተባበር ስሕተትና ለጉዳዩ ሰብሳቢና ኃላፊ አካል መሆንን አለማወቅ ነው፤

እንግዲህ ይህንን ለማድረግ ምንድነው የጐደለን ወይም ያቃተን ያልን እንደሆነ እያወቁ እንዳላ

ወቁ፤ እያሰቡ እንደማያስብ ሆኖ መገኘታችን ብቻ ነው፤ ከእዚህም ሌላ ሁሉም ቅን አሳቢ የሆነ እየመሰለው በየበኩሉ የሚፈጥረው የሃሣብ ልዩነትና በተለየም የእውነተኛን ቅን አሳቢዎች ስሜት ያልተረዳ ሆኖ የራሱን አስተያየት ቅን አሳብ ብሎ ይዞ የሌላውን መንገድ በክፉ የሚመለከትና ወይም ክፉ ያደርሰል፤ ሊያደርስ ነው ብሎ በመሥጋት ቅን አሳቢ በመምሰል ሳይወድ በየዋህነት የሌላውን ወገን ነቃፊና አጭበርባሪ አድርጐ በመገመትና በማየት ሲያሳጣና ሲያጣላ ይገኛል። እንደዚህ ያለውም ከፍተኛ ስሕተት ከዚያው ትክክለኛ ካልሆነው ያለመተባበር ጉድለት ሞልቶ ተርፎ የሚፈስ ለመሆኑ አያጠራጥርም። እኛው ለእኛው በምንሠራው ነገር መለግም አይኑርብን፤ እራሳችንም አስተካክለን ለመምራት ስናውቅና በአለንም አቅም መተዳደርና በዘዴም መሻሻል ስንችል ዓይኖቻችን እያዩ፤ ጆሮቻችንም እየሰሙ፤ ሁላችንም በምንቸገረኝነት የምናሳልፋቸው ጊዜዎች እንደገና እየሠሩብን አሁንም ከድንቁርና ማጥ ሳንወጣ ያንኑ እያበሳን ስንዳክር ከተገኘን ከለመግባባትም የተነሣ የሚፈጠረው ተውሳክ የሀገርና የሕዝብ ማጥፊያ ጠንቅ አስከትሎ ያንኑ የጠላነውንና ወደኋላ አስቀረን የምንለውን የእርስ በእርስ መፋጀት አድሶ፤ የሰው እንጅ የሀብትና የመሬት ደህ ያልነበረችውን ሀገራችንን አሁንም የሰው ደህ አድርጐ እንዳያስቀራት ያሠጋል፤ ይህም ብቻ ሳይሆን የባዕድ ሲሣይ ለመሆን መጋለብ ይቅር፤ አሳብ ጽኑም እንሁን፤ የሀገራችንንም ጉዳይ በቀደምት እንመልከት እንጅ፤ ሆነ ተብሎ የሚፈጠሩትን ማለያያዎች እያ

ጐላን በሕዝቡም ዘንድ ተሰራጭተው ሰላም እን ዲነሡና ዕረፍት እንዲያሳጡ እያደረግን የምንነዘቸ ው ሐሰቶችና ቅጠቢስ ዝናዎች ሁሉ የአራሳችን መጉጃ መሣሪያዎች መሆናቸውን እንወቅ ። በተለ የም የባዕድ አንደበቶች የሚተፉቸውን ውሸቶች በየመጽሔቱ መመልከትና ያንንም አምኖ እያባዙ በመተረክ እራስንም በመጠራጠር ውስጥ እያስዋኙ መገኘትና መወላወል፤ ያልሆነውንም የማይረባ ነገር እያራቡ በተንኰል ተመርቶ፤ ሀገርን ሕዝብን ወደ ውርደት መገፋፋት፤ ያንኑ ያለውን የየግል ትዳር እ ንደዚሁም የማኅበራዊ ዕድገትንና ኑሮን ለማፍረስ መጣጣር ከአእምሮአችን ውስጥ ይሠረዝ ። በሥል ጣን ላይ የሚገኝ ሁሉ የገባበትን ቃል ኪዳን አክ ብሮ አስታውሶም ሀገሩንና ሕዝቡን፤ ማኅበራዊ ኑሮ ን እንጅ ክብሩንና ሥልጣኑን አገልጋይ አይሁን ።

ቀደም ካለው ትውልድ የምመጣ ስለሆንኩ በ ሀገራችን የሆኑትንና ያለፉትን የደረስኩባቸውን አ ጥርቼ ስለምረዳው የነበረውንና ያለውንም ሳመዛ ዝነው እደረስንበት ሥፍራና ደረጃ እንደምን እንደሆነ በበኩሌ ደህና አድርጌ አገነዘበዋለሁ ።

ይኸውም የሀገር ፍቅር አቃጥሎአቸው ደማቸ ውን ባፈሰሱት ብዙሀን ትጋትና ዕውነተኛ መስዋዕ ትነት መሆኑ አይካድም ። ባለታሪክ የሆኑት አባቶቻ ችን፤ የነበረባቸውን ትግልና ድካም፤ የውስጥ ተቃ ዋሚ ወገንንና የውጭ ጣልቃ ገብ የባዕድ ፖሌቲካ በትዕግሥት አልፈው የገነቧትን ሀገራችንን ዘቅርቡ ተወልደው፤ ደርሰው፤ ያዩአት እንዲሁ ሆና የቆየ ች ትመስላቸው ይሆናል ። የደረሱበትንም እንደአ

ቅሙ የተደላደለ ጊዜ ከመንቀፍ በፊት፤ እንዴት ኖሯል ብሎ ወደኋላ የነበረውን ጠይቆ፤ ተረድቶ፤ ያለውን አመስግኖ ስለመጭው መሻሻል ትጋትን አ ሳይቶ የአሳብ ተካፋይና የሥራ እረዳት ሆኖ በትጋት ማከናወን የእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ፈንታ ስለሆነ ማንኛውም የሀገሪቱ ዜጋ በተሠማራበት የሥራ መስክ ዕውቀትና ጉልበቱን መስዋዕት ማድረግ ይኖርበታል ።

መሥራት አስቸጋሪ ነው ማፍረስ ግን በጣም ቀላል ነው ።የፈረሰን ደግሞ መልሶ መሥራት ከሁሉ የበለጠ አስቸጋሪ ነው ያንን የተከፋፈለ አሳብ ያንን የተወሳሰበ መጥፎ ልማድ ፣ ያንን የተጨቆነ የሕዝብ መብትና ነፃነት ፣ያንን የተናቀ የገዥና የተገዥነት መንፈስ ለማጥፋት ፣እንደዚሁም ፈርሳና ወድቃ የነ በረችውን ውድ አገራችንን እንደገና ለማቋቋምና ከነባ አህጉሮች ጐን እንድትሰለፍ ያደረጓት ሁሉ ባለውለታዎች ናቸው ።በእዚህ በአጭር አነጋገር ሊመዘገብ የማይቻለው ሰፊ ታሪካቸው የቱን ያህል እንደሆነና በኢትዮጵያችን ተወራራሽ ትውልድ ዘንድ ሲለመሰግናቸው እንደሚኖር አያጠራጥርም

ስለእዚህም በዕድሜ ዘመናችን ዓይናችንን ከከፈትነው፤ አንዳንዳቸን ያልተደረገውን ወደሌላ በ መተርጐምና ውለታ ቢሶች ሆነን ከመገኘት እርቀን ለሁላችንም ለሀገራችንም የሚበጀውን ብቻ በፍቅ ርና በጎብረት አስማምተን ተደጋግፈንም እፊታችን የተደቀነውን የትዬሌሌ ተያይዘን በጊዜአችን ልናደ ርገው የምንችለውን ያህል እንወጣው ።

ስለ ሃገራችን ክብር የተሰውትንም፤ አጽማቸ

ውም በያለበት የረገፈውን ጀግኖቻችንን ሁልጊዜ እናስታውሳቸው፤ ስማቸውም በታሪክ ጐልቶ እንዲኖር እናድርግ፤ ውለታቸውም ይወሳላቸው፤ ምንም ጀግናን የሚፈጥረው ጊዜና የጊዜው ሁናቴ ነው ቢባልም፤ አዲሱ ጊዜ የሚፈጥረው ጀግና የቀድሞው ጊዜ ጀግና ስምና ታሪክ መነሻና መቀስቀሻ እንደሚሆነው አያጠራጥርም።

እንግዲህ ከዚያም ከዚያም ጠቅሼ የደረደርኳቸው እዚህ ጽሑፍ ውስጥ የሠፈሩት አነጋገሮች ሊነቀፉም ሊያስነቅፉም ሊያከራክሩም ይችሉ ይሆናል፤ ነገር ግን በማንኛውም ዓይነት ይሁን በንጹሕ ሐሊና ብቻ በመመራት ወደፊትም የሚጠብቀንን በመገመት ማንኛችንም ተባብረን ለውድ ሀገራችን የእውነት አገልግሎት ማበርከት እንዳለብን ማሳሰቤ ነውና «አውቀን እንታረም»።

መ ድ ረ ሻ።

በመነሻው ከሞላ ጐደል እንደገለጽኩት ሁሉ እንግዲህ የእኛ ነገር «ዘሮ ዘሮ ከቤት፤ ኖሮ ኖሮ ከመሬት» እንደሆነ ደህና አድርገን እናውቃለን፤ ስለዚህም ዘረን ዘረን የምንገባበትን ሀገራችንን ቤታችንን፤ ኖረን ኖረን የምንቀበርባትን መሬታችንን እንደዋዛ አንያት። ሁላችንም ነገ ጥለነው ለምንሄደው ነገር አንጓጓ፤ ሀገራችን ካልን የሃገራችን ነገር ከሁሉ በፊት ይቅደም ሃገራችንን ካልን ደግሞ ይዘን እናሽታግራት፤ እንጠብቃት፤ ክልብም እንውደዳት፤ አንድነትም ሆነን እናገልግላት፤ ከእኛ በኋላ ለሚመጡትም ሀገራቸው ሆና እንድትቆይ፤ እንድትወራረስም አድርገን እንያዛት

ሰው በሰው ክፉ መሆን አይገባውም፤ በተለየም የአንድ ሀገር ሰዎች፤ የአንድ እናት ልጆች ማለት ነንና መተዛዘንን፤ መተሳሰብንና መፈቃቀርን ማወቅ ግዴታችን አድርገን እንያዘው።

ወንድም በወንድሙ ላይ በስንቱ አይነሣ፤ የስንቱ ነገርንም ምንጮች አይቆፍር። እያንዳንዱም ለቅ አፉን ይክፈት፤ በጐ ምግባርንና የሀገር ፍቅርን ከመናገር፤ ከመስበክ አይቦዝን።

ሁላችንም እናልፋለን፤ ይህንን የማያምን ቢኖር የነበሩ እነማን አሉ? ማለፋችንን ከመን ስለምን በቀና መንገድ አንሄድም? ስለምንስ ቅን ሠርተን አናልፍም?

ይኸ ሁሉ ከንቱ ይኸ መውጣት መውረድ
በዓለም ላይ ነኝ ብሎ ተዝናንቶ መረመድ
እነ መንፈላሰስ እነምን አለብኝ እነ መንቀባረር
ሁል ጊዜ እሸት ሆነው ሁል ጊዜ አዲስ ነገር
ሲቀርቡት ሲታዩት ሰው ሁሉ ሲሻቸው
ግማሹ ሲቀበል ሌላው ሲሸኛቸው
ብርቅ መስለው ሲመጡ ሲመላለሱ አይቶ
መስገብገብ መሻማት ለሚሄዱት ትቶ
ለምኞት መገዛት ላልታመነ ተስፋ
ለሚበን አዋራ ታይቶ ለሚጠፋ ።

አ. አ.